



"በለቅሶ የሚዘሩ በደስታ ይለቅማሉ ።
በሔዱ ጊዜ ዘራቸውን ተሸክመው እያለቀሱ ተሠማሩ
በተመለሱ ጊዜ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው
ይመጣሉ" መዝ. 125 ቍ. 5-6

# ትንሣኤ




ዮሴፍና ድንግል ማርያም ለተወለደው ሕፃን በበረት ውስጥ ማረፊያ ሲፈልጉ።

ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም | ቁጥር ፬ | ታኅሣሥ ፲፱፻፸ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

''ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረ ጉሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ ''ትንሣኤ'' ተብሎ ተሰይሟል ።

አዘጋጅ

**ነቅዓ ጥበብ ወንድም**

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት

የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ

በሁለት ወራት አንድ ጊዜ

እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616

የመልእክት ሣ.ቁ. 3137

አዲስ አበባ

# ደብዳቤዎች

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
አዲስ አበባ

መስከረም 1 ቀን 1970 ዓ.ም. በወጣው በቁጥር 8 ትንሣኤ መጽሔት ብዙ ጠቃሚ ነገሮች አይቻለሁ ። ለምሳሌም ያህል 1/ ቤተ ክርስቲያን የማናት ፤ 2/ ሴቶች በሃይማኖት ፤ 3 ቤተ ክርስቲያንና እኩልነት የሚሉትና ሌሎችም ናቸው ። ግን ይህንን ደብዳቤ ሊያጽፈኝ ያስገደደኝ ነገር ቢኖር ወጣቱ ትውልድ ቤተ ክርስቲያን የምታወጣቸውን መጽሔፍት ቁም ነገር ያላቸው ስለማይመስለት ነው ።

ታዲያ በዚህ መጽሔት ላይ ወጣቱን የሚስብ ሃይል መኖር አለበት ። ለዚህም መሳቢያ ይሆናል ብዬ እኔ ያሰብኩት የወጣቱን ፎቶግራፍ እስከነ አስተያየቱ ማውጣቱ ነው ። ለዚህ ደግሞ የገቢ ምንጭ ከየት ይገኛል ይባል ይሆናል ። ገቢውን ማለት በመጽሔቱ በኩል ያለውን ቤተ ክህነት ትቻል ። እለበለዚያም በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት በዓመት የተወሰነ ገንዘብ እንዲያዋጡ ቢደረግ የተሻለ ይመስለኛል ። ለምሳሌ በኢትዮጵያ 5000 (አምስት ሺ) አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩ ከስለት ገቢያቸው ብቻ በዓመት ከፍተኞቹ $60.00 ዝቅተኞቹ $30.00 እንዲከፍሉ ቢደረግ በጠቅላላው $210.000 (ሁለት መቶ አሥር ሺህ) ብር ይገኛል ይህም ለወጣቱ ክልሽ ቢሆን ጥሩ ነው ብዬ ሃሳቤን እደመድማለሁ ።

ሕፃን ዘሩባቤል ዘለቀ
ዕድሜ 9 ዓመት ከ4 ወር
የትምህርት ደረጃ 8ኛ ክፍል
አድራሻ የማኅደረ ስብሐት ቅድስት ልደታ የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር
ፖ.ሣ.ቁ. 5300
አዲስ አበባ

ሕፃን ዘሩባቤል ዘለቀ አስተያየትህ የሚደገፍ ነው ሁሉም እንዳንተ ያለውን አሳብ ጥቆማ ቢያደርግ ቤተ ክርስቲያናችንን ወጣቱ ትውልድ ሊርቃት ባልቻለ ነበር ። የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር በጣም በርከት ያለ ነው ። ችግሩ ብዛት ሳይሆን የሚፈለገው ጥራት በመሆኑ እንተ ለምሳሌ ያቀረብካቸው አብያተ ክርስቲያናት ምዕመናን ቢሆኑ ሌላም ባላስፈለገ ነበር ።

ለወጣቱ ክልሽ ቢሆን ያልከው እኛም በአስተሳሰብህ ተስማምተንበታል ቋሚ ክልሽ ይሁን ብለናል ።

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በአሁኑ ዓመት ለሁለት ወር ለመስከረምና ለጥቅምት ያወጣችሁትን የትንሣኤ መጽሔት ከዳር እስከዳር አንብቤዋለሁ ። መጽሔቱ መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን ሥጋዊውንም የያዘ በመሆኑ እኔን እንደሳበኝ ሌሎችንም እንደሚስብ እገምታለሁ መጽሔቱን ብተችው የስተኞች ናችሁ ?


መጽሔቱ ርእሱና በውስጡ ያሉት ቃላቶች ጥሩ ሆነው ሳለ የእያንዳንዱ ዳቸው ርእስ ረጅም በመሆኑ ይኸውም ጽሑፍ ማለቱነው እኔን እንዳሰለቸኝ ሌላውንም የሚያሰለች መሰለኝ የመጽሔቱ አዘጋጅ አንተስ ምን ይመስልሃል እኔ አጠር አጠር ቢል ጥሩ መሰለኝ ።

በሌላ በኩል ደግሞ መጽሔቱን የማመሰግነው ሴቶች የጽሑፍ ተባባሪ ሆነው በማየቱ ሐይኸውም ከታሪኳ ምስክር ሴቶች በ ሃይማኖት በሚል ርእስ የተጻፈው ጽሑፍ የበሰለ ሆኖ ስላገኘሁት ነው የበሰለ ነው ያልኩበት ምክንያት ሴቶች በጥንታዊው የጣዖት መቅደስ ምን ያህል ጭቆና እንደነበረባቸውና በሃይማኖት ስበብ ግፍ ይፈጽምባቸው እንደነበረ ግልጽ አድርጋ ስለጻፈች ነው ወይፊትስ ይህን የመሳሰለውን ጽሑፍ እንድትጽፍ የመጽሔቱ አዘጋጅ ትጋብዛታለህ ? እንደእ አስተያየት እሷንም ጋብዛት ሌሎችንም ሴቶች የጽሑፍ ተካፋይ እንዲሆኑና መንፈሳዊነትም እንዲሰማቸው ብትጋብዛቸው መልካም ነው ።

የሴቶች ተሳትፎ የሌለበት ማንኛውም ሥራ አልሙኡ ስለማይሆን የትንሣኤ መጽሔት ተካፋይ እንዲሆኑ ጥሪ ብታደርግላቸው መልካም ነው ይህ ከሆነ መጽሔቱ ብዙ አንባቢ ሊያገኝ እንደሚችል እርግጠኛ ነኝ አመሰግናለሁ ።

አድራሻዬ ቅድስት ማርያም
አዲስ አበባ
እቴነሽ ረጋሣ
ፖ.ሣ.ቁ' 30786

ድርጅቱም የሚፈልገው ምስጋና ብቻ ሳይሆን ነቀፋና አስተያየት ጭምር ነው በደብዳቤው ላይ የሠፈረውን ሁሉ ተቀብለነዋል እንደ ነታሪኳ ምስክር ያሉትን እንዲጽፉ መልእክትሽን አስተላልፈናል እንቺና መሰሎችሽም ለሴቶች ዓምድ የሚሆን ጽሑፍ እንደማትነፍጉን ተስፋ አለን ።



የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ጽ ቤት ከሚያካሒዳቸው የሥራ ዘርፎች አንዱ የሥጋጃ ሥራ ነው ።

ካቴድራሉ ለዚህ ሥራ ብቁ የሆኑ ሠራተኞች አሠልጥኖ በማሠራት ላይ ይገኛል ። የሥጋጃዎቹም ዓይነትና መጠን ፈላጊዎች ባቀረቡት መሠረት እንደሚሠራ የሥራው ባለሞያዎች ያረጋግጣሉ ።

በአሁኑ ጊዜ ካቴድራሉ ችግር ሆኖ ያገኘው የተሠሩት ሥጋጃዎች ባለመሸጣቸው የዚህን ክፍል ሥራ እንቅስቃሴ ወደኋላ የሚጐትት መስሎ ታይቶታል ።

ስለዚህ የቤተ ክርስቲያናችን ድርጅት ስለሆነ ምዕመናን የሆናችሁ ሁሉ ቢቻል ለመግዛት ባይቻል ግን የሚሸጥበትን መንገድ ብትጠቁሙን ቤተ ክርስቲያናችሁን እንደረዳችሁ ይቆጠራል ።

የመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሥጋጃ ክፍል
የስልክ ቁ. 120170
የፖ.ሣ.ቁጥር 3137
አዲስ አበባ

አርእስት ማውጫ ገጽ

'ርዕሰ አንቀጽ' ....................2
ቅዱስ ሲኖዶስ ....................3
ሰላም በምድር ....................4
ጥያቄዎች ....................5
የመንደር አስተማሪዎች ውለታ ....6
ልማት ኮሚሽን ....................8
"ኃይል የእግዚአብሔር ጦር የጌዶ ዎን" ....................10
ሽፍኑ ሰውነት ....................13
'ዜና አብያተ ክርስቲያናት ..........15
ከእናት ትቫል ምግዚት ..........
አብያተ ክርስቲያናት ድርቅን ሲቋቋሙ ..16
"ተስፋህ ከማትፈጽም ባትሳል ይሻላል" ...17

www.ethiopianorthodox.org




ብዙ ሰዎች በየቀኑ እንዴት አደራችሁ ? እንዴት ዋላችሁ ? የሚለውን የሰላምታ ቃል ትተው ሰላም!!
ሰላም !! በመባባል የእጅ ሰላምታ ይለዋወጣሉ ነገሩ መልካም ነው ። ችግሩ የአፍ ብቻ ስለሚሆን ብዙዎቹ
የመንፈስ ሰላም አይታይባቸውም ።
ሰላም የተናጋው ከመጀመሪያው ሰው ጀምሮ በመሆኑ በአንድ ሰው የገባው ኃጢአት የሰው ልጆችን
ሁሉ ሰላም አሳጥቷቸው ለብዙ ዘመናት በሥቃይ እንደኖሩ ቅዱሳት መጻሕፍት ይናገራሉ ። ይሁን እንጂ
ጊዜው ሲፈጸም ጌታ ኢየሱስ ስለዓለም ሰላም በመወለዱ ''በጨለማ ውስጥ ላሉ ሁሉ ብርሃን ወጣላቸው''
ተብሎ እንደተጻፈው በሰይጣን አገዛዝ ተረግጠው የነበሩ ሁሉ በክርስቶስ ልደት ሰላምን አግኝተዋል ።
በጌታ ልደት ተራርቀው የነበሩት ሰዎችና መላእክት በደስታ ተውጠው ''ክብር ለእግዚአብሔር በአ
ርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ'' እያሉ በአንድነት አመስግነዋል ክርስቶስ ስለሰዎች ሰላ
ምና ደኅንነት በመወለዱ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው ጥላቻ ተወግዷል ።
ስለዚህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለተከታዮቹ ሲያስተምር ''በምትገቡበት ቤት ሁሉ አስቀድማች
ሁ ሰላም ለዚህ ቤት በሉ በዚያም የሰላም ልጅ ቢኖር ሰላማችሁ ያድርበታል አለዚያም ይመለስበታል'' ሲል
የተናገረው ጠብና ጭቅጭቅ እንዳይኖር ለማስጠንቀቅ ነው ።
ሌሎችም ከዚያው ወዲህ የተነሡት ስለሰላም ብዙ አስተያየት ሰጥተዋል ። አንድ ሊቅ ሲናገር ''በራ
ሱ ግላዊ ሕይወት ፍጹም ሰላም በሌለው ሰው ሰላም ሊገኝና ሊስፋፋ አይችልም'' በማለት ከልብ ሳይሆን የአ
ፍና የእጅ ሰላምታ የሚለዋወጡትን ግብዞች ሲመክር አንድ የምሥራቅ ሊቅም ስለተባበሩት መንግሥታት
ሸንጐ ሲናገር ''በተባበሩት መንግሥታት አገራቸውን ወክለው የሚሰበሰቡት የሰላም ልኡካን እርስ በርስ
እየተከፋፈሉ ከመነታረክና ከመጨቃጨቅ ይልቅ ተባብረውና አንድ ልብ ሆነው ስለዓለም ሰላም ቢደክሙና
ቢታገሉ ኖሮ ጦርነት በጭራሽ ጠፍቶ ዓለማችን የፍትሕና የሰላም መድረክ በሆነች ነበር'' ሲል ተናግሯል ።
አዎ የሰላም መልእክተኞቹ ስለ ዓለም ሰላም ቢጥሩ በቬትናም ሰላም ጠፍቶ 30 ዓመታት ሙሉ የጦር
ነት እሳት በሰላማዊው ሕዝብ ላይ ባልነደደም ነበር ዛሬም ሰላም ፈላጊ በሆነችው በኢትዮጵያ የድንበር ማስ
ፋፋትን የሚሹ የሰላም ጠንቆች ሰላሟን ለማደፍረስ ባልተነሣሱም ነበር ። በመሠረቱ እንዲህ ያሉትን ዕብሪ
ተኞች ሰላም ወዳድ የሆኑ አህጉርና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የሰላም ጉባዔ በዝምታ ሊመለከቱተው አይ
ገባም እንግዲህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምትገቡበት ሁሉ ሰላም ለዚህ ቤት በሉ ባለው መሠረት እያንዳንዳ
ችን ዓለም ሰላም ያገኘችው በክርስቶስ ልደት መሆኑን አምነን የመንፈስ ሰላም እንድናገኝ ለጌታችን ኢየሱስ
ክርስቶስ ሁልጊዜ በአፍ ብቻ ሳይሆን ከልባችን ''ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላም በምድር
ለሰውም በጎ ፈቃድ'' እያልን እንዘምር የክርስቲያኖች የሰላም መሪያቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና ።



# ቅዱስ ሲኖዶስ ስድስት ሊቃነ ጳጳሳት ተጨማሪ ሥራ እንዲሠሩ ወሰነ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ከተቋቋመ ጀምሮ እስከ አ ሁን ድረስ ያሳለፋቸው ውሳኔዎች በሥራ ላይ እንዳልዋሉ የአሁኑ ዓመት የጥምቀቱ ቅዱስ ሲ ኖዶስ መርምሮ ከተረዳ በኋላ ከፓትርያርኩ ሥር ሆነው ልዩ ልዩ መንፈሳውያንን ጉዳዮች እንዲፈጽሙ ስድስት ሊቃነ ጳጳሳት ተሹመ ዋል ።



በውሳኔው መሠረት ፡

1ኛ ብፁዕ አቡነ ቄርሎስ የኢሉባቦር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ህዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ጽ ቤት የአስተ ዳደሩ የበላይ ተጠሪ ፡



2ኛ ብፁዕ አቡነ ማርቆስ የጎጃም ሀገረ ስብ ከት ሊቀ ጳጳስ በኢ/ ኦርቶ/ ተዋሕዶ ቤተ ክርስ ቲያን ጠቅላይ ጽ/ቤት የሥነ ጽሑፍ፣የማስታወ ቂያና የሊቃውንት ጉባኤ መምሪያ የበላይ ተጠ ሪ ፡



3ኛ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ የከፋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በኢትዮ/ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ሲና ዶስ ዋና ጸሐፊ ፡



4ኛ ብፁዕ አቡነ አብርሃም የሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጠ ጽ ቤት የት ቤቶች የበላይ ተቆ ጣጣሪ ፡





6ኛ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የባሌ ሀገረ ስብ ከት ሊቀ ጳጳስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የውጭ አብያተ ክርስቲያናት ግንኙ ነት የበላይ ተጠሪና የልማት ኰሚሽን ሥራ አስፈጻሚ ሆነው እንዲሠሩ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡ ነ ተክለ ሃይማኖት ፓትሪያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳ ሳት ዘኢትዮጵያ የተፈቀደ መሆኑን ከኢትዮጵ ያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ጽ/ ቤት የተገኘው ዜና አመልክቷል ።

የቤተ ክርስቲያናችንን ችግር የሚያውቁት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በሹመት ላይ ሹመት ጨ ምረው እንዲሠሩ ቅዱስ ሲኖዶስ መወሰኑ ያስ መሰግነዋል ። ምክንያቱም አባቶቻችን የብዙ ዓመታት የሥራ ልምድ ስላላቸው የዛሬዪቱን ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ተሐድሶ ለማጠና ከር ጊዜ ስለማይፈጅባቸው ውሳኔውን አሁ ኑኑ በሥራ ላይ እንደሚያውሉት ተስፋ እናደር ጋለን ።

5ኛ ብፁዕ አቡነ እንድርያስ የጐንደር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከት ፡ የሰበካ ጉባኤ ፡ የገዳማትና የአድባራት የበላይ ተጠሪ ፡



www.ethiopianorthodox.org

# ሰላም በምድር

"ሰማይ ስማ ምድርም አድምጪ እግዚአብሔር ተናግሯልና"

ይህ እንግዳ አነጋገር አንድ ጊዜ አንድ የታወቀ ታጋይ ነቢይ መስማት ያለባቸውን ቃል ይሰሙ ዘንድ የዘመኑን ሰማይና ምድር ያዳኘበት የማሳሰቢያና የማስጠንቀቂያ መልእክት ነበር ። ተናጋሪው ነቢዩ ኢሳይያስ ሲሆን ለማለት የተገደደውም በምድር ላይ ሰላም በሰላም እንዴት ለመሥራት እንደሚችል የሚያስተምር የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ስለሆነ ባለበት ኃላፊነት ሰላምና ሰላም ፈላጊዎች ሁሉ ሲገናኙ የሚችሉበትን መንገድ ለማመልከት ነው ።

ነቢዩ ኢሳይያስ በታወቀው የትንቢት መጽሐፉ መጀመሪያ ላይ "ሰማይ ስማ ምድርም አድምጪ ''ሲል ሰማይና ምድርን ያማጸነበት ይህ በአንድ በኩል በእግዚአብሔር ዘንድ የማይሰማ የማይሰማ ግዑዝ ነገር አለመኖሩን የሚገልጽ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ "ሰማይና ምድር'' የሚለው ቃል "ትሑትና ልዑል' ወይም የበላይና የበታች የሚለውን ዘይቤ በሌላ ቃል ለመግለጽ የሚያገለግል ኅቡዕ ስም ስለሆነ በጊዜው በነበረው ኅብረተ ሰብእ መካከል የነበረውን የኑሮ ልዕልናና ትሕትና ለመግለጥ ያህል በዚህ እንጻራዊ ስም ለመጠቀም መገደዱን ያመለክታል ።

ሰላም የሰው ልጆች ሁሉ የማይለወጥ ምኞትና ፍላጎት እንደ መሆኑ መጠን የዚያን ጊዜው ሰማይና ምድር ወይም ልዑላንና ትሑታንም እንዲሁ ሰላም ፈላጊዎች ነበሩ ። ነገር ግን በሁለቱ መካከል ይፈጸም በነበረው ሰው ሰራሽ አመጽ ምክንያት ሰላም ከእነሱ የራቀች ስለ ነበረች ነቢዩ እነዚያን የእግዚአብሔርን ቃል ያዳምጡ ዘንድ የጋበዛቸውን ሰማይና ምድር

**"ከፉ ማድረግን ተው ፤**
**መልካም ማድረግን ተማሩ ፤**
**ፍርድን ፈልጉ ፤**

**የተገፉውን አድኑ (፩ ፡ ፲፯) ሲል ሰላምን በሰላም ለመመሥረት በቅድሚያ ዐረ ሰላም የሆኑ ግብራቸውን እንዲተው ከመከረ በኋላ ትንቢታዊ መልእክቱን በመቀጠል ይህ እንዲህ ከሆነ ያን ጊዜ በምድር ላይ ያሉ ሁሉ ።**

**"ሰይፋቸውን ማረሻ ፤ ጦራቸውንማ ጭድ ለማድረግ ይቀጠቅጣሉ ፤ ሕዝብም በሕዝብ ላይ አይነሣም ሰልፍም ከዚያ ወዲያ አይማሩም ፪፡፬" ሲል ይመጣ ዘንድ ያለውን ዘመን ሰላምና በምድር ላይ ይመሠረት ዘንድ የሚጠበቀውን ሥርዓተ ማኅበር ያበሥራል ።**

አዎ ይህ መቼ እንደሚሆን ነቢዩ ጊዜ አልወሰነም ። እሱ የጠቆመው ብቻ ሰዎች ሁላቸው በማንኛውም ጊዜ ራሳቸው በመጀመሪያ መሆን የሚገባቸው ከሆኑና ማድረግ የሚገባቸውንም ካደረጉ ያን ጊዜ ሊኖር የሚገባው ሰላምና ሰላማዊ ኑሮ ያለ ችግር ሊኖር እንደሚችል ነው ። ሁኖም ንጽሐጠባይዕ ያደፈበትን የሰው ልጅ ወደቀድሞ ሕይወቱ ለመመለስና ለዚህ ዓይነቱ ተግባርም ምሳሌነት ያለው አንድ የሰላም መሪ ያስፈልግ ነበር ። ስለዚህ በዚያች ሰዓት ነቢዩ ኢሳይያስ ይህ ወደ ፊትይሆን ዘንድ ያለው ደገኛ ምሥጢር ተገልጾለት ።

"አለቅነቱ በጫንቃው ላይ የሆነ ስሙ ድንቅ መካር
ኃያል አምላክ
የዘለዓለም አባት
የሰላም አለቃ "ተብሎ የሚጠራ አንድ ሕፃን እንደሚወለድ (፱፡፮) ትንቢት ተናገረ ። እሱም ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

ክርስቶስ በእርግጥ የሰላም መሪ በመሆኑ በልደቱ ቀን "ምስጋና ለእግዚአብሔር በሰማይ ሰላምም በምድር ይሁን" የሚል የምሥራች ዜና በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰምቷል ። በኋላም የሰላም ወንጌልን በሚያስተምርበት ጊዜ ስለ ሰላም የሰጠው የመጨረሻ መመሪያ " ሲላው ለእናንተ ሊያደርግላችሁ የምትፈልጉትን እናንተም ለሌላው አድርጉ ሌላው በእናንተ ላይ ሊያደርግባችሁ የማትፈልጉት እናንተም በሌላው ላይ አታድርጉ''የሚል ነበር በሰዎች መካከል ፍጹም የሆነ ሰላምን ለመፍጠር ከዚህ የተሻለ ሥርዓትባለመኖሩ የነበረውም ሆነ ያለው እንዲሁም ወደ ፊት የሚኖረው ትውልድ የፈለገውን ያህል ቢመራመር ከቶ ከዚህ የተለየ የሰላም መንገድ ሊያገኝ አይችልም ሌላውንእንደ ራስአለማየትና ራስን ከሌላው አልቆ መውደድ በሰዎች መካከል ለሚፈጠረው ሁሉ አለመግባባት ዓይነተኛ መንስኤ ስለሆነ ይህ እስከ ሆነ ድረስ ለሰላም የሚደረገው ጥረት ሁሉ ሊሠምር አይችልም እያንዳንዱ ሰው ይህን የማኅበራዊ ኑሮ መሠረታዊ ሕግ በትክክል ከፈጸመ ግን "ሰላም በምድር' የሚለውም ቃል ያንጊዜ በግብር ሊገለጥ ይችላል ። የሰላም አለቃ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በአንድ በኩል "በምድር ላይ ሰላምን ለመስጠት የመጣሁ አይምሰላችሁ ሰይፍን ማለት መለያየትን እንጂ ''(ሉቃ.፲፪፡፶፩) ሲል እያስጠነቀቀ በሌላ በኩል ደግሞ "ሰላም ለሁላችሁ! ሰላሜን እሰጣችኋለሁ ሰላምን እተውላችኋለሁ (ዮሐ.፲፬፡፳፯) በማለት ይናገር የነበረው ስለዚህ ነበር።

የዓለም ሁኔታ እንደሚያስረዳው የነበረውም ሆነ ያለው ዓለም አቀፍ ሰላም ሁለት ዓይነት መልክና ጠባይ ያለው ነው ። ይኸውም አንደኛው ዓይነት የፍቅርና የወንድማማችነት ሰላም ሲሆን ሌላው ደግሞ የፍርሐት ሰላም ነው ይህ ከሆነ ዘንድ የሰላም ፈላጊዎችም ዓይነት እንዲሁ በሁለት የተከፈለ ስለሆነ አንደኛው ክፍል የሚከተለው መመሪያ "ሰላምን ከፈለግህ ለጦርነት ተዘጋጅ'' የሚል ከመሆኑ የተነሣ በዓለም ላይ የፍርሐት ሰላምን ይመሠረት ዘንድ ለሰው ሕይወት ጠንክ የሆኑ መሣሪያዎችን በመፈልሰፍ ለኃያልነት ሲሽቀዳደም ሌላው ክፍል ግን የሚመኘው በሰዎች መካከል በፍቅርና በወንድማማችነት ላይ የተመሠረተ ሰላም ይሰፍን ዘንድ የሰልፍ ሰዎች ሁሉ ሰይፋቸውን ወደ ማረሻ ጦራቸውን ወደ ማጭድ እንዲለውጡ ነው የጦር መሣሪያ እንዲቀነስና ፈጽሞም እንዳልነበር ይሆን ዘንድ ነው ምክንያቱም የፍርሐት ሰላም ዘላቂነት ሊኖረው ስለማይችል የሰው ልጅ የመጨረሻ ፈራ ባለመሆኑ አንድ ቀን ፍርሐቱ ወደ ድፍረት ሲለወጥ ያን ጊዜ ያ በፍርሐት ላይ የተመሠረተ ሰላም ድንገት እንዳልነበር ከመሆን ይደረሳል አቸናፊም እንደገና ተቸናፊ ሊሆን ይችላል የፍቅርና የወንድማማችነት ሰላም ግን እሱ ኃያልና ዘለዓለማዊ ነው እውነተኞችና ትክክለኞች ሰዎች የሚመርጡት እውነተኛው ሰላምም ይኸው ነው ።

በአሁኑ ጊዜ "የኖቤል ሽልማት'' ጌ የተባለ የሚጠራውን የሰላም ሽልማት ድርጅት ያቋቋመው ኖቤል በመጀመሪያ ለሰው ሕይወት ጠንክ የሆነ የዲናሚት ፋብሪካ ባለቤት ነበር በኋላ ግን በዚህ በሚፈላሰፈው አደገኛ መሣሪያ በመካትፈንታእንዲያውምለኀሊናውሰላምን ስለነሣው በዚህ መሣሪያ ሽያጭ ያገኘውን ገንዘብ እንደገና በሕዝቦች መካከል የወንድማማችነት መንፈስና ሰላም እንዲሰፍን ተግቶ ለሠራ ወይም ደግሞ የጦር ኃይል እንዲቀነስ ወይም ጨርሶ እንዲቀር ለጣረ ወይም የሰላም ጉባዔ እንዲጸና ለደከመ ሁሉ በሽልማት መልክ እንዲሰጥ ወስኖ ለማለፍ ተገድዷል ይህም የሚያመለክተውየመጨረሻው ተፈላጊ የወንድማማችነት ሰላም ብቻ መሆኑን ነው በነቢዩ አንደበት የተነገረው አምላካዊ ቃልም የሰልፍ ሰዎች ሁሉ ሰይፋቸውን ወደ ማረሻ ጦራቸውን ወደ ማጭድ ይለውጡ ዘንድ ያሳሰበው ስለዚህ ነበር ።

ሁኖም ሰዎች የሰላምን አስፈላጊነት የሚገነዘቡት አደገኛ ሥራቸው የራሳቸውን የውስጥና የውጭ ሰላም የሚነሣ ሁኖ ሲገኝ ብቻ ከሆነ እንዲህ ያሉትን ወገኖች "የሰላም ሰዎች'' ብሎ መሰየም ያስቸግራል በመሠረቱ አንድ ሰው "የሰላም ሰው'' ሊባል የሚገባው የሚያስበውም የሚሠራውም ሁሉ የሰላም መሣሪያ ሲሆን ነው ስለዚህ ክርስቶስ በቃሉም በተግባሩም ፍጹም ምሳሌነት ያለው በእርግጥ የሰላም አለቃ ስለሆነ እናከብረዋለን እናገንዋለን ።''

ሰላም ራሱ ጽድቅ ነው ጽድቅም ሰላም ነው ሰዎች በምድር ላይ በሰላም መኖር ከቻሉ ይህ ዓለም ለእነሱ ገዜያዊ የተድላ ገነት ነው አይሁድ በተስፋ ይጠብቁት ስለነበረው መሢሕ ከፍተኛ ተመስጦ የነበረው አንድ ዘርጅል የተባለ ሮማዊ ባለቅኔ ክርስቶስ ሳይወለድ ከጥቂት ዓመታት አስቀድሞ በጻፈው ቅኔ በዘመኑ ወርቃማ የጽድቅ ጊዜ የሚሆንበት ስለአንድ ሕፃን መወለድ ተናግሮ ነበር ይህም የሰላምና የጽድቅ ጌታ ስለሆነው መድኅን ክርስቶስ ልደት የእግዚአብሔር መንፈስ በአሕዛብ አንደበት ሳይቀር የተናገረው ትንቢት ነበር ።

ይህ ብቻ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ መወለድ በዘመኑም ይገለጥ ዘንድ ስለአለሙ አዲስ የሰላምና የጽድቅ ዓለም ከቶ ያልተነገረ ትንቢትና ያልተመሰለ ምሳሌ የለም ትንቢቱም ምሳሌውም በክርስቶስ ልደት ተፈጽሟል ። ክርስቶስ "አቸናፊ ፍርዱ ድል እስከ ምትነሣ ድረስ አሕዛብም በስሙ ተስፋ እስኪያደርጉ ድረስ የተቀጠቀጠ ሸምበቆን አይሰብርም የሚጤስ የጧፍ ኩስታሪንም አያጠፋም'' ማቴ.፲፪፡፳) ተብሎ ስለእሱ የተነገረውን ትንቢት በትክክል የፈጸመ በእርግጥ የሰላም መሢሕ ነው ።

ስለዚህ የዓለም ክርስቲያኖች ሁሉ በአሳባቸውም በሥራቸውም በቃላቸውም "ሰላም በምድር''እያሉ የክርስቶስን ልደት ያከብራሉ ፤ አርአያውንም ይከተላሉ ። መላክ ታቦር ተሾመ ዘርይሁን

## ጥያቄዎች

አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ

ልጆቻቸው ወንድሞቻቸው የሆኑ የማን ልጆች ናቸው?

2- ኢየሱስ ናትናኤልን ወደእርሱ ሲመጣ ባየው ጊዜ ምን ብሎ መሰሰለት?

3- ኢየሱስ መጀመሪያ ያደረገው ተአምር ምን ነበር?

4- ኢየሱስ በኢያሪኮ ሲያልፍ ወደማን ቤት ገባ?

5- ፊልጶስ ከጀንደረባው ጋር እንዲገናኝ ማን ላከው?

6- እግዚአብሔር ለኖኅ ቃል ኪዳን በገባ ጊዜ የቃል ኪዳኑን ምልክት በምን ሰጠ?

7- ይስሐቅ ማለት በአማርኛ ሲተረጎም ምን ማለት ነው?

8- ማርያም ሕፃኑን በምን ውስጥ አስተኛችው ?

9- ኢየሱስ 12 ዓመት ሲሆነው ወደየት ሄደ?

10-እግዚአብሔር የማያርገውን አልሆ ውርም ያለው ማንን ነው?

ከላይ የተጠቀሱት ጥያቄዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪካቸው ስለሚገኝ እስከ ሦስት ጊዜ ድረስ በተከታታይ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች በቂ መልስ የሰጠ አስፈላጊ ሽልማት ያገኛል የሽልማቱ ዓይነት በሚከተለው መጽሔታችን ይገለጣል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት የስልክ ቁጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁጥር.3137 አዲስ አበባ





www.ethiopianorthodox.org

# የመንደር አስተማሪዎች ውለታ

በሀገራችን በየክፍለ ሀገሩ ፤ በየወረዳውና በየቀበሌው እንደዛሬው የዘመናዊ ትምህርት ሳይቋቋም ማንኛውም ሰው ፊደል ቆጥሮ የማንበብና የመጻፍን ጥበብ የሚገበየው በየቤተ ክርስቲያኑና በየመንደሩ በግል ፈቃዳቸው በሚያስተምሩ መምሕራን አማካይነት እንደ ነበረ ግልጽ ነው ።

በየትም ቦታ የመምሕራን ማሰልጠኛ ት ቤት በሌለበት በዚያ ጨለማ ዘመን መምሕራኑ በትምሕርት ላይ ሳሉ ምንም የሚረዳቸው ድርጅት ወይም መንግሥት አልነበረም ። በዚያ ድንቁርና በሰፈነበት አስቸጋሪ ዘመን ለዚህ ዓይነቱ መንፈሳዊ ዓላማ ድርሻዋን ያበረከተች ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነበረች ።

የቤተ ክርስቲያኒቱም አባሎች የሆኑት ምዕመናን "በእንተ ስማ ለማርያም" እያሉ ለምነው ለሚማሩት የቆሎ ተማሪዎች አስፈላጊውን ምግብ በመስጠት ርዳታቸውን ሲያበረክቱ ኖረዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለሚፈልጉት ተማሪዎች ስታበረክት የኖረችው ርዳታ ሁለት ዓይነት መሆኑን ከዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ይመስለኛል ፤ ይኸውም በመጀመሪያ ደረጃ ነፃ ትምህርት መስጠት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተማሪው በትምህርት ላይ ሳለ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተዘዋወረ በተዝካር ፤ በዝክርና በሰንበቴ እህል ውኃ ከመረዳቱም በላይ ከቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ዘንድ በልመና መልክ በሚሰጠው ርዳታ ቀለቡንና ልብሱን ችሎ መማሩ ነው ።

ከብዙኃኑ ሕዝብ እጅ ርዳታ እያገኙ ይማሩ የነበሩት ጥንታውያን ተማሪዎች የሚገበዩትን ዕውቀት ከእንቅብ ውስጥ እንዳለ መብራት አዳፍኖ የማስቀረት ልማድ የላቸውም ። ምንም እንኳን ደመወዝ የሚከፍላቸው ድርጅት ባይኖር ''ያለዋጋ ያገኛችሁትን ያለዋጋ ስጡ'' ተብሎ ከታላቁ መምሕር ክርስቶስ የተነገረው ቃል መመሪያቸው ስለሆነ የማስተማር ሥራቸውን በዛፍ ጥላ ሥር ይጀምሩና ያላቸውን ዕውቀት ለወገኖቻቸው እያካፈሉ መኖርን ይመርጣሉ ።



የሀገራችን ሊቃውንት የተማሩ በዚህ ዓይነት ነው ።



በቀድሞው ሥርዓተ ትምህርት ማንኛውም ተማሪ ማስተማር የሚጀምረው ትምሕርቱን ከፈጸመ በኋላ ብቻ ሳይሆን ገና በትምሕርት ቤት ሳለ ስለሆነ ልምምዱንም የሚያጠናቅቀው በዚያው ነው ። ለምሳሌ ንባብ የሚያውቀው ፊደል ሲያስቆጥር ዳዊት የደገመው ደግሞ ንባብ ያስነብባል ማለት ነው ። ከፍተኛ ደረጃ ደርሰው ዜማና ቅኔ ወይም የመጻሕፍት ትርጓሜ የሚማሩ ተማሪዎችም ቢሆኑ በወንበራቸው ከመምሕራቸው እየተማሩ ተራ እስኪደርሳቸው ደግሞ በዕውቀት ከነሱ ዝቅተኛ ለሆኑት የሚያውቁትን ለማያውቁት ያስተምራሉ ፤ ይህ የፈቃድ ብቻ ሳይሆን ግዳጅም ጭምር ስለሆነ ለያንዳንዱ ተማሪ በተዋረድ የማስተማር ተራ ይደርሰዋል ማለት ነው ። በዚህ ጊዜ የማስተማር ልምዳቸውና ፍላጎታቸው እየሰፋ ስለሚሄድ ትምሕርታቸውን ከፈጸሙም በኋላ ያላቸው የማስተማር ልምድ ስሜታቸውን ስለሚቀሰቅሰው በገዛነው መቀመጥን አይፈልጉም ። በደረሱበት ቦታና መንደር ሁሉም ቾትና መዝናናትን ሳይሹ የማስተማር ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ፍላጐታቸው ያስገድዳቸዋል ።

በየቤተ ክርስቲያኑና በየመንደሩ ሲያስተምሩ የኖሩት ጥንታውያን መምሕራን ደመወዝ ባይኖራቸውም ማስተማሩን እንደጸሎት ስለሚቆጥሩት ወንበራቸው የሚታጠፈው ወደቤተ ክርስቲያን በሚሄዱበትና እህል ውኃ በሚቀምሱበት ጊዜ ብቻ ነው ። ከምሽቱም እንኳን ግማሹን ሌሊት የሚያሳልፉት የቃል ትምሕርት በማስተማር ነው ። ደመወዝ የለሾች እንደመሆናቸው መጠን አንዳንዶች የሚያስተምሩት የተግባረ ዕድና የግብርና ሥራ እየሠሩ ስለሆነ በእጃቸው ሲጽፉ በቃላቸው ቃለ እግዚአብሔር ይናገራሉ ። እያረሙና እየቆፈሩ ወይም እንጨት እየጠረቡ የማስተማር ሥራቸውን ላለማቋረጥ ሲሉ አንደበታቸው ከማስተማር የሚቦዝንበት ጊዜ የለም ። በሌላ በኩል ደግሞ ከማስተማር በቀር ሥራ መሥራትና መተዳደር ለማይችሉት መምህራን ተማሪዎቻቸው እየለመኑ እያበሏቸው የማስተማር ሥራቸውን ሳያቋርጡ እድሜያቸውን ፈጽመው ወደ መቃብር ዓለም የወረዱ እጅግ ብዙዎች ናቸው ።

ምናልባት ለአንዳንዶቹ መልካም ዕድል ገጠማቸው ቢባል በሚያስተምሩበት አካባቢ የሚገኘው ሕዝብ ቀለብ እየሠፈረላቸው የዕለት ጉርሳቸውን የዓመት ልብሳቸውን የሚያገኙ መምሕራን በሚታዩበት ጊዜ ነው ። ያለዚያም ያላቸው ሌላው ዕድል ተማሪዎች በትርፍ ጊዜያቸው በጉልበታቸው እየረዷቸው ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ምርት ከማምረት የግብርና ሥራ እየሠሩ በማስተማር ወገንን መርዳት ይሆናል እነዚህም ድርጊቶች አሁንም በአንዳንድ ገጠር አገሮች ሲፈጽሙ የሚታዩ ስለሆኑ እንደ ታሪክ የምናወሳቸው ብቻ ሳይሆኑ በዓይናችንም ያየናቸው ናቸው። በኑሮ በኩል ይደርስባቸው የነበረውን ሁኔታ ስንመለከት ቤትና ንብረት የነበራቸው መምሕራን እጅግ በጣም ጥቂት ስለነበሩ አብዛኛዎቹ በየመቃብር ቤቱና በየደጀ ሰላሙ ራሳቸውን አስጠግተው የሚኖሩ ናቸው ። በዚህ ዓይነቱ ጉስቋላ ኑሮ እየኖሩ ለኅብረተሰቡ ይሰጡት የነበረው ጥቅም ግን በሚዛን የሚመዘንና በሜትር የሚለካ ሳይሆን በተጠቃሚው አእምሮና በታሪክ የሚቀረጽ ነው ። ይህም "ጧፍ እየነደደ ለሌላው ብርሃን ይሰጣል" የሚባለውን ምሳሊያዊ አነጋገር ያስገነዝባል ። ከዚህ ችግር ጋር ተስፋ እንዳይቆርጡ በኔታ ጉሮሮ ጠጅ ይንቆርቆር በሚል ቃል ተማሪዎቻቸው ያጽናኗቸው ነበር ከዚህም ሌላ እንደጨረቃ ያድምቅዎ እንደወርካ ያስፋዎ እንደ ቁጤማ ያለምልምዎ መንግሥተ ሰማያት ያውርስዎ" እያሉ ያሞኳሿቸው ነበር ይህም የሚያመለክተው በተማሪዎቹና በመምህራኑ መካከል ያለውን መግባባትና ፍቅር ነው ።

በቀድሞ ዘመን ጸሐፊው ፤ ዳኛው አገር አስተዳዳሪውና ማንኛውም ሁሉ እንደነዚህ ካሉት መምሕራን ሀ ፤ ሁ ብሎ ፊደል የቆጠረና በዚህ ዓይነት ደረጃ የሠለጠነ ነበር ። አሁንም ቢሆን በየከተማው ባሉ መንደሮች ውስጥ ተሰራጭተው በማስተማር ላይ የሚገኙት የመንደር አስተማሪዎች በዓቅማቸውና ባላቸው ዕውቀት መጠን ለሀገሪቱ የሰጡት ጥቅም በዋጋ የሚተመን አይደለም ፤ በልዩ ልዩ ሞያ ሠልጥነው በየሥራ መስኩ ተሠማርተው የሀገሪቱን እንቅስቃሴ በሥልጣኔ ጐዳና ለመምራት በመጣጣር ላይ የሚገኙት ምሑራን ሁሉ በሕፃንነታቸው ወራት በመንደር አስተማሪዎች አማካይነት የፊደልን ቅርጽ ለይተው ካወቁ በኋላ ነው ወደ መንግሥት ት ቤቶች ገብተው ለከፍተኛ የዕውቀት ደረጃ የበቁት ። በአሁኑ ጊዜ በየትምህርት ቤቱ በመማር ላይ የሚገኙት ወጣቶች በመጀመሪያ አእምሯቸውን የሳሏቸውና የእውቀትን ውጋጋን እንዲያዩ ያደረጓቸው በየሠፈሩ ያሉ መምሕራን ስለሆኑ አሁን የሚገኙበት ት ቤቶች መድረሻቸው እንጂ መነሻቸው አይደሉም ። በየሠፈራቸው ካሉ የመንደር መምሕራን ዘንድ ቢያንስ ፊደል ፤ አቡጊዳና ወንጌል ሳይቈጥሩ ወደመንግሥት ት ቤት የገቡ ቢኖሩ እጅግ በጣም ጥቂቶች ና በጣት የሚቆጠሩ ናቸው ። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያችን ውስጥ ማንበብና መጻፍ ይችላል ብለን የምንተምነው እነዚሁ የመንደር አስተማሪዎች ያስተማሯቸውን አጠቃለን በመደመር ነው ።

የመንደር አስተማሪዎች ለሕዝቡ እጅግ ከፍ ያለ ጥቅም የሰጡ ሲሆን ለራሳቸው ግን የሚያገኙት ጥቅም ከድካማቸው ጋር የሚመጣጠን አይደለም ። ከዚህም የተነሣ፤ በኑሮዋቸው ከወትሮዎቹ መምሕራን የሚሻሉ አይደሉም ፤ ከነዚያ የሚለዩበት ነገር ቢኖር የቅድሞዎቹ በመዋጮ እህል ሲተዳደሩ የዛሬዎቹ ደግሞ ከየልጁ 0.50 ሳንቲም ፤ ቢበዛ አንድ ብር በወር እየተቀበሉ ከእጅ ወደአፍ የሆነ ኑሮ መኖራቸው ነው ሌላው ዘመናዊ ትምህርት በማስተማሩ በየወሩ እስከ 500 ብር እየተከፈለው በክብር ሲኖር የጥንታዊና ብሔራዊ ትምሕርት አስተማሪዎች ሆነው ሕዝቡን



www.ethiopianorthodox.org

# የኢ.ት ኦር ተዋ ቤተ ክርስቲያን የልማት ኮሚሽን ለምን ተቋቋመ ?

ባለፈው ጽሑፍ ላይ ኮሚሽኑ ምን እንደሠራና እንደሚሠራ ወደፊት በተከታታይ እናቀርባለን ባልነው መሠረት በአሁኑ እትም ከኮሚሽኑ አንጋፋ እቅዶች መካከል አንደኛው የሆነውን የካህናት ማሰልጠኛ ፕሮግራም እንመለከታለን ።

የልማት ኮሚሽን የካህናት ማሠልጠኛ ፕሮግራም እንዴት ተጀመረ ?

የተቋቋመበትስ አላማ ምን ነበር ?

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የልማት ኮሚሽን በሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 415 1964 ዓ.ም. ከታኅሣሥ 26 ቀን 1964 ዓ.ም ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ውስጥ ራሱን የቻለ መሥሪያ ቤት በመሆን እንደተቋቋመ በመጀመሪያ ያተኰረው ቤተ ክርስቲያናችን ባላት የሰው ኃይል በልማት ረገድ ለሀገሪቱ ምን አስተዋጽኦ ለማበርከት እንደምትችል ማጥናት ነበር ።

ለጥናቱም ፍንጭ የሰጠው በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙት ከ15.000 በላይ የሆኑት አብያተ ክርስቲያናትና ከ200.000 በላይ የሆኑት ካህናት ቁጥር ነበር ። የካህናቱ ቁጥር ቀላል ባለመሆኑ የተነሣ እነዚህን በአስፈላጊው ሙያ በማገባ እሠልጥኖ ለልማት ሥራ እንዲሠማሩ ቢደረግ ኮሚሽኑ ለሚተልማቸው ዓላማዎች አንቂና ቀስቃሾች እንደሚሆኑ ፡ ለሀገሪቱም በልማት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማበርከት እንደሚችሉ በመታመኑ በእቅዱ እንዲገፋበት ተደርጓል ።

ይልቁንም ካህናት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በማኅኛውም ሥፍራ የሚገኙና ያላቸውም ተሰሚነት ከፍተኛ በመሆኑ የሀገሪቱን የልማት እንቅስቃሴ በይበልጥ ለማፋጠን ዓይነተኛ መሣሪያዎች እንደሚሆኑ በመታመኑ በመጀመሪያ እነርሱን ማስተማርና በተራቸው ደግሞ መልሰው ሕዝቡን እንዲያስተምሩ ፡ ሕዝቡም መብትና ግዴታውን ዐውቆ እንዲጠቀምበት ሲረዱ በአጭር ጊዜ ጥሩ ውጤት እንደሚገኝ ርግጠኛ ጉዳይ ሆኖ በመገኘቱ ፕሮግራሙ ፦

ሀ ሕዝብን ለማስተባበር

ለ በተግባረ ዕድ

ሐ በመምህርነት

መ በእርሻ የትምህርት ዓይነቶች ላይ በማተኮር ዘመናዊ ትምህርት እንዲሰጥ ተደረገ ። የፕሮግራሙ ዘላቂ ዓላማ የኢትዮጵያን ካህናት በሙሉ በተገቢው የሙያ ዓይነቶች አሠልጥኖ በሥራ ላይ እንዲውሉና እያንዳንዱም ቤተ ክርስቲያን ከመንፈሳዊው አገልግሎት ጋር የልማት ማሠልጠኛ ጣቢያ እንዲኖረው ለማድረግ ነበር።

በዚህ እምነት በዝርዝር ተነድፎ በጥናት ከተረጋገጠ በኋላ ለእርዳታ ሰጪው ድርጅት (የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የልማት ክፍል ተልኮ በሥራ ላይ እንዲውል ለፕሮግራሙ መጀመሪያ የሚሆነው በጀት ስለተፈቀደ ማሠልጠኛው በቅዱስ ጳውሎስ ት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ በጥገኝነት በጥቅምት ወር 1965 ዓ.ም. የመጀመሪያውን ፕሮግራም እንዲጀምር ተደረገ ።

2. ማሠልጠኛው በፕሮግራሙ ያተኮረባቸው የትምህርት ዓይነቶች

የማሠልጠኛው ፕሮግራም በመጀመሪያው እቅዱ ያተኮረባቸው የሙያ ዓይነቶች እላይ የተዘረዘሩት ነበሩ ።

ስለዚህም በግብርና የሚተዳደሩ ካህናት በእርሻ ሙያ በማስተማር ላይ ያሉት በአስተማሪነት ፡ በደብር አለቅነትና በሰባኪነት የሚያገለግሉት ሕዝቡን በማስተባበርና በመምራት ፡ በዕደ ጥበብ ልምድ ያላቸው ደግሞ በተግባረ ዕድ ሙያ እንዲሠለጥኑ ተደርጓል ፤ ካሕናቱ በጤና አጠባበቅ እንዲሠለጥኑ ታስቦ በተግባር ላይ ሳይውል ቀርቷል ።

አሁን ያለው የካህናት ማሰልጠኛ ለሙከራ የተጀመረ ሲሆን ፡ በረጅም ጊዜ እቅድ መሠረት መናገሻ ላይ እስከ 500 ካህናት በአንድ ጊዜ ተቀብሎ ለማወሠልጠን የሚችል ትልቅ ኢንስቲትዩት ለመሥራት ከዓለም ባንክና ከዩኒስኮ ጋር ስምምነት ተደርሶ በውጥን እንዳለ መቅረቱ ታውቋል ።

ማሠልጠኛው ለአራት ዓመታት ያህል በተሰጠው ዓላማ መሠረት ካህናትን ሲያሠለጥን ቆይቶ ፡ ከ1969 ዓ.ም. ጀምሮ ግን ዓላማውን ለውጦ እንዲሠራ ተደርጓል ።

3. የመጀመሪያው የማሠልጠኛ ፕሮግራም እንዲቀየር ለምን አስፈለገ ?

ከዚህ በፊት የትምህርቱ ዓላማ እንዲያተኩር ተደርጎ የነበረው በዚያን ጊዜ፦

ሀ ካህናት በሕዝብ ዘንድ ያላቸውን ተደማጭነት በመመልከት ራሳቸውን ረድተው ኅብረተሰቡንም በይበልጥ ሊያገለግሉ የሚችሉበት የሙያ ትምህርት እየሰጡ በማሳማራት ፡

ለ በነበረው የኢኮኖሚ ሥርዓት ቤተ ክርስቲያንም እንደሌላው ሁሉ የምትተዳደርበት እንደመሬት የመሰለው ቋሚ ንብረት ስለነበራት ይበልጡን የሕዝቡን ኑሮ በማሻሻል ፡

ሐ የገጠሩም ሆነ የከተማው ሕዝብ እንደ አሁኑ በማኅበር ስላልተደራጀ ካህናት ሕዝብን በማስተባበር ረገድ የልማት ሥራዎች ተሳታፊና ቀስቃሽ እንዲሆኑ በማድረግ ላይ ሲሆን ፤ አሁን ግን በእነዚህ ሁኔታዎች ላይ መሠረታዊ ለውጥ በመደረጉ ፤

መ/ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ጊዜ ከተዕዕኖ ነፃ የሆነ የውስጥ አስተዳደር ባዲስ መልክ እንድትመሠርት ዕድል የማግኘቷን ያህል ራሷን የሚያስችላት አቋም እንዲኖራት ማድረግ አስፈላጊና ከሌላው የበለጠ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ በመሆኑ ፤

ሠ ከዚህ በፊት ሰልጥነው የወጡት ካህናት የሚጠበቅባቸውን ያህል የሥራ ውጤት ሊያሳዩና ትምህርቱም የተተለመለትን ግብ በታሰበው መጠን ሊመታ ያልቻለው በየሰበካው የሚገኙ ካህናትና ምዕመናን በአዲስ መንፈስ ኅብረታቸውን አጠንክረው ተደራጅተው የቤተ ክርስቲያናቸውን ህልውና ማረጋገጥ የሚችሉበት የሰበካ ጉባዔ አስተዳደር በየሥፍራው ባለመቋቋሙና ባለመጠናከሩ ስለሆነ ፡ የቀድሞው ፕሮግራም እንዲለወጥ አስፈለገ ።

ከላይ በተጠቀሰው መሠረት አዲሱ ፕሮግራም የሚያተኩረው በሰበካ አስተዳደር ትምህርት ላይ ሲሆን ካህናቱም የሰበካ ጉባዔዎችን ለማቋቋም ፤ ለማጠናከርና ለማደራጀት በሚችሉበት ዘዴ እንዲሠለጥኑ ጥረት ይደረጋል ።

በዚህ መሠረት የሠለጠኑት ካህናት ፦

- የሰበካ ጉባዔዎችን በአጭር ጊዜ በየአብያተ ክርስቲያናቱ እንዲቋቋሙ ፡
- ምዕመናን ከመቼውም ይልቅ በአሁኑ ጊዜ በደንብ ተደራጅተው ቤተ ክርስቲያንን በሐሳብ በጉልበት ፡ በገንዘብና በመሳሰሉት ሊረዱ እንዲችሉ ማነቃቃትና ማስተባበር ፤
- የቤተ ክርስቲያን ህልውና እንዲጠበቅና ለምዕመናኑ የምትሰጠው አገልግሎት በዘመናዊ መልክ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲካሄድ ፡
- ካህናት በትምህርት ፡ በተግባር ፡ በጠባይና በመሳሰሉት በቂዎች ሆነው በመገኘት ከምዕመናኑ ጋር በመተባበር አገልግሎት እንዲያበረክቱ ፡ ለማስቻል ፡
- ንዋየ ቅድሳት ፤ መጻሕፍት ፤ ከሥዕሉት የሚገኙ ገቢዎችና የመሳሰሉት በሚገባ እንዲጠበቁ ፡
- የታሪክ ቦታዎች የሆኑ ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ገቢ በሚያስገኙበት አኳኋን ተደራጅተው እንዲጠበቁ ፡
- የአካባቢያቸውን ምዕመናን በማስተባበር ደረጃ አብያተ ክርስቲያናትን የማስጠገን እንደ አስፈላጊነቱም አዲሶችን የማሠራት ፡
- ካህናቱ ራሳቸው የተሻለ የኑሮ ደረጃ እንዲኖራቸው እና የመሳሰለውን የማድረግና የመፈጸም ኃላፊነትና ግዴታ ይጠበቅባቸዋል ።

4. እስካሁን ስንት ካህናት ሰለጠኑ ? ምን ምንስ ተጨባጭ ሥራ ሠሩ ?

ኮርሱ ከተጀመረበት አንስቶ እስከ 1969 ዓ.ም. መጨረሻ ድረስ በጠቅላላው 447 ካህናት በተለያዩ የሙያ ዓይነቶች ሠልጥነው ተመርቀዋል ።

ኮርሱን ፈጽመው ወደየክፍለ ሀገራቸው ከተመለሱት ካህናት መካከል ጥቂቶቹ በሠለጠኑባቸው የሙያ ዓይነቶች ተጨባጭ ሥራዎችን የሠሩ መሆኑ ቀደም ሲል ከተደረገው ክትትል ለማወቅ ተችሏል ። ለምሳሌም ያህል በእድዋ የፈትል ሥራ ማኅበር ፡ በመቀሌ የሸማ ሥራ ድርጅት ፤ በባሕር ዳር የስጋጃ እንዱስትሪ ያቋቋሙና በተለያዩ ክፍለ ሀገሮች የውሃ ጉድጓድ ያስቆፈሩ ፡ መንገድ ድልድዮች የሠሩ ፡ ወፍጮዎች ያስተከሉ ፤ ት/ቤቶች እየከፈቱ የሚያስተምሩ ፤ የሰበካ ጉባዔዎችን ያቋቋሙና ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት ላይ ያሉ በእርሻም ሙያ በኩል አካባቢያቸውን ከዘመናዊ የእርሻ ዘዴ



በትምህርት ሳይኰሎጂ ክፍለ ጊዜ ካህናቱ ትምህርቱን በተመስጦ ሲከታተሉ ፡



ካህናቱ በክፍል ውስጥ የሚያሳዩት ተሣትፎና የትምህርት ፍላጐት ከፍተኛ ነው ።

---

## የመንደር አስተማሪዎች .....

ሲያገለግሉ በየወሩ የሕፃናት እጅ እያዩ አምጣ አታምጣ በሚል ንትርክ ቅስማቸው ተሰብሮ አንዱ ሲሰጣቸው ሌላው እየቀማቸው በሄደ ቊጥር የብስጭትና የንቀት ኑሮ መግፋት ነው ።

በቀድሞ ጊዜ "አንድ ቀለም የነገረህ እንደአባትህ ፤ ሁለት ቀለም የነገረህ እንደፈጣሪህ" የሚለው አነጋገር ለማንኛውም መምህር ከፍ ያለ ሞራልና ደስታ ከመስጠቱም በላይ በአስተማሪነታቸውም ሲመኩበት ኖረዋል በአሁኑ ጊዜ ግን ያ ሁሉ ተረስቶ ለመምህሩ "ቄሱ" የሚል የንቀትና የፌዝ ስም ሲሰጠው ፡ በየመንደሩ ያሉትንም ትምህርት ቤቶች "የቄስ ትምህርት ቤት" በሚል የንቀት አጠራር እየጠሩ ያንኳስሷቸዋል ። «እህል ላበደረ አፈር ፤ ወርቅ ላበደረ ጠጠር» እንዲሉ ሕፃናት በለሰለሰ አንደበታቸው «የኔታ» እያሉ ፊደል ቆጥረው ካደጉና ለከፍተኛ ደረጃ ከበቁ በኋላ የሚከፍሉት ውለታ ምስጋና ሳይሆን የዚሁ ተመሳሳይ ነው ፤ ምንም እንኳን "ቄስ" ማለት የእግዚአብሔር አገልጋይ ማለት በመሆኑ ያሳፍራል ባንልም ከኮሶ ጋር ከደባለቁት ማርም እንኳን ይመራልና ካለባቸው የኑሮ ዝቅተኛነት ጋር በዚህ ምክንያት ሞራላቸው እንዳይወድቅና ቅስማቸው እንዳይሰበር መጠንቀቅና መምሕራኑ ወደፊት ተሻሽለው ለራሳቸውም ሆነ ለሚያስተምሯቸው ሕፃናት በይበልጥ ጠቃሚ እንዲሆኑ ማሰብ ያስፈልጋል ።

በየመንደሩ ያሉ አስተማሪዎች ውለታ ከታወቀ ዘንድ 1ኛ/ እንደሌላው ሁሉ ኮርስ እየተዘጋጀላቸው በየክረምቱ ወራት ሠልጥነው ተጨማሪ ዕውቀትና ሥልጣኔ እንዲያገኙ ማድረግ ፤

2/ ለሠራተኛ ዋጋ ይገባዋል ተብሏልና መምሕራኑ ከመዋጮ ፍራንክ ድነው በወር ደመወዝ የሚተዳደሩበትን ዘዴ መፈለግ ፤

3ኛ/ የሚያስተምሯቸውን ሕፃናት በጤናቸው በኩል ለመንከባከብ እንዲያመች በየፈሰሱ እየተንፋቀቁ ፀሐይ ከሚያቃጥላቸው ይልቅ ጽዳታቸው እንዲጠበቅ የሚማሩበት ክፍልና መቀመጫ እንዲዘጋጅላቸው ማድረግ አስፈላጊ ስለሆነ በየከተማው የተቋቋሙት የቀበሌ ማኅበራት ቢያስቡበት መልካም ነው እንላለን ።

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ





www.ethiopianorthodox.org

ጋር በማስተዋወት መልካም ምሳሌዎች የሆኑ እንዳሉ ይታወቃል ። እነዚህ ለምሳሌ ያህል ተጠቀሱ እንጂ የተመረቁት ካህናት የሠሯቸው እነዚህ ብቻ ናቸው ለማለት አይደለም ። ካህናቱ ከላይ ከተጠቀሱት የማያንሱ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለኅብረተ ሰቡና ለራሳቸውም የሚጠቅሙ ብዙ ተጨባጭ ሥራዎችን ፣ እንደሠሩና በመሥራት ላይም እንደሆኑ አያጠራጥርም ።

### 5. ማሠልጠኛው በተቋቋመበት ዓላማ መሠረት ግቡን መቷል ወይ ?

በአጠቃላይ ለመናገር ያህል ትምህርቱ በማሠልጠኛው ፕሮግራም የተሳተፉትን ካህናት በአመለካከታቸው ፣ በአስተሳሰባቸውና በአሠራራቸው በጣም እንዲሻሻሉ የረዳቸውና የጠቀማቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል ። ለምሳሌም ያህል ከማሠልጠኛው የተመረቁት ካህናት በቤተ ክህነትና በአብያተ ክርስቲያናት በሚዘጋጁ ሰሚናሮችና ስብሰባዎች ላይ እየተወከሉ ተልእኮአቸውን በሚገባ ፈጽመዋል ። በቤተ ክህነት ውስጥ ለከፍተኛ ሥራ የተመረጡና በኃላፊነት ላይ ያሉ ብዙ ናቸው ።

ከዚህም በላይ ማሠልጠኛው ለቤተ ክርስቲያን በመንፈሳዊና በዓለማዊ ትምህርትና በተለያዩ ሙያዎች የሰለጠኑ የሰው ኃይል ማበርከቱ በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ አይደለም ።

በማሠልጠኛው ውስጥ ከሠለጠኑ በኋላ ምንም ዓይነት ሥራ ያልሠሩ ፣ እንዳውም የተማሯቸውን የሙያ ዓይነቶች በተግባር ለማዋል እንዲረዷቸው የተሰጡአቸውን ውድ ዕቃዎች እንኳን ሳይጠቀሙባቸው የቀሩ እንዳሉ የማይካድ ነው ። ዳሩ ግን ይህ ተስፋ የሚያስቆርጥ ሳይሆን የሚዘጋጁትን የኮርስ ዓይነቶች የቤተ ክርስቲያንን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት በማድረግ እንድናደረጃቸው ማስጠንቀቂያና ትምህርት ሆኖናል ።

ከዚህም የተነሳ ማሠልጠኛው የቀድሞውን ፕሮግራም ለውጦ በአሁኑ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ ነው ተብሎ በሚታሰበው የሰበካ አስተዳደር ትምህርት ላይ እንዲያተኩር ለማድረግ ዓላማውን እንዳስፈላጊነቱ ማሻሻል ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል ።

### 6. ማጠቃለያ

የካህናት ማሠልጠኛ ፕሮግራም ምንም እንኳን የኮሚሽኑ አንጋፋ የሥራ እቅድ ቢሆንም አወጣጡን ለሙከራ ስለሆነ አሁንም በሙከራ ላይ ነው ያለው ቢባል ስህተት አይሆንም ። ለዚህ ድጋፍ የሚሆነው የቀድሞው ፕሮግራም በጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት መለወጡና በሌላ የትምህርት ዓይነት እየተፈተነ መሆኑ ነው ። ሌላው ደግሞ የዚህ ፕሮግራም ጠቃሚነትና አስፈላጊነት ከሚፈለገው ደረጃ ሲደርስ ማሠልጠኛው እየተስፋፋ የሚሄድ መሆኑ ነው። ይህም ምናልባት ከዚህ ቀደም በተወሰኑ ቦታዎች ተጨማሪ የካህናት ማሠልጠኛዎችን ማቋቋም አስፈላጊነት ወይም በየክፍለ ሀገሩ እንዲጀመሩ ታስቦ ለነበረው መፈጸም ምክንያት ይሆን ይሆናል ብለን እናምናለን ።

ማሠልጠኛው ከዚህ ቀደም ካህናትን በአራት የሙያ ዓይነቶች ሲያሠለጥን ቆይቶ ዓላማውን በመለወጥ የተለየ ትምህርት በማስተማር ላይ ያለ መሆኑ ተገልጿል ። ለምን መለወጥ እንዳስፈለገ ተዘርዝሯል ። በተጨማሪም የሙያውን ትምህርት ማሠልጠኛው መቀጠል የሚያስፈልግበት ምክንያት አለ ።

የተግባረ ዕድን ሙያ በቅርቡ ተቋቁሞ ሥራውን የጀመረው የጐፋ ገብርኤል የዕደ ጥበብ ማሠልጠኛ ት ቤት በማካሄድ ላይ ስላለ ይህን በደንብ ማስፋፋትና ማጠናከሩ ስለሚጠቅም ፣ በእርሻም በኩል ያለው ሁኔታ እንደዚሁ በመንግሥት በኩል ተገቢው ርምጃ በመወሰዱ እምብዛም አያሳስብም ። ሕዝብን የማስተባበሩንም ሙያ ከሰበካ አስተዳደር ትምህርት ጋር ተጠቃሎ እንዲቀርብ ተደርጓል ። የመምህርነቱም ሙያ ቢሆን እንደዚሁ በተፈለገው ሁኔታ እየተዘጋጀ ለቤተክህነት መምህራን በመስጠት ላይ መሆኑ ከሐምሌ 1 ቀን 1969 ዓ.ም. እስከ ነሐሴ 30 ቀን 1969 ዓ.ም. ድረስ የተካሄደው ኮርስ በቂ ማስረጃ ነው ። ለሰባክያንም የሚያስፈልገው በቂ ዘመናዊ የስብከት ዘዴ በትምህርቱ ፕሮግራም ውስጥ አስቀድሞ ስላለ አያሳስብም።

ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ ማሠልጠኛው የሰበካ አስተዳደር ጉባኤዎችን የሚያቋቁሙ ፣ የሚያጠናክሩና እያደራጁ የሚያስፋፉ ካህናትን እንዲያሰለጥኑ ማድረጉ ተገቢ ይሆናል ። ምናልባት ለዚህ ተግባር የሚፈለገው የሰው ኃይል በቂ ከሚሆንበት ደረጃ ላይ ሲደርስ ለዚያም እንደ ጊዜው ተጨባጭ ሁኔታ ሌላ ለቤተ ክርስቲያንና ለአገልጋዮቿ የሚጠቅም የትምህርት ዓይነት ማዘጋጀት በሚያስፈልግበት ጊዜ ፕሮግራሙን ወደሌላአቅጣጫእንዲያተኩርለማድረግየሚያዳግት ነገር አይኖርም ።

# “ኃይል የእግዚአብሔር ጦር የጌዴዎን”

ይህ መንፈሳዊና ጀግንነት የተዋሐደው ቃለ መፈክር በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አለንበት ክፍለ ዘመን ድረስ አያሌ ዓመታት አልፈዋል ፣ መንፈሳዊ ቃልን የጊዜ ብዛት ፣ የዘመን እርቀት ስለማይገታው ቃሉን በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፎ ስንመለከተው ሁልጊዜ አዲስ እየመሰለ እናገኘዋለን ። ቃሉ እስከ ዛሬ ኑሯል አሁንም አለ ፣ ወደፊትም እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ እንደሚኖር አይጠረጠርም ።

ቀደም ብለው በዘመን አራት የነበሩ ሕዝቦች ክብራቸውን ለማዋረድ ነፃነታቸውን ለማሳጣት ሰላማቸውን ለማደፍረስና አንድነታቸውንም ለመከፋፈል ጠላት በተነሣባቸው ጊዜ ድል እናደርጋለን ብለው የሚተማመኑት ከጦር መሣሪያቸውና ከጀግንነታቸው ጋር በእግዚአብሔር ኃይል ነበር ።

ከታሪክ እንደምንረዳው እስራኤላውያን ወደ ጦር ግንባር በሄዱ ጊዜ የእግዚአብሔር ስም የተጻፈበትን ታቦት ይዘው ይዘምቱ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ የእስራኤል ሕዝቦች ኃይለ እግዚአብሔር ይረዳናል ብለው የሚተማመኑት በጦርነት ጊዜ ብቻ አልነበረም ። የእግዚአብሔር ስም በተጻፈበት ቦታ አማካይነት ፈሳሹ የዮርዳኖስ ውሃ ቆሞላቸው በደረቅ ለመሻገር በቅተዋል ።

በዘመን አበውም ሆነ በዘመነ መሳፍንት በዘመነ ነገሥትም ሆነ በዘመነ ካህናት በሀገር ወሰንና ደንበር መጣላትና መዋጋት እንደ ፈሳሽ ውሀ ሊታገድ የማይቻል ዓቢይ ተግባር ነበር ፣ ሆኖም አጠቃለሁ ብሎ የተነሣው ሲጠቃ ኃይለኛው ሲደክም ፣ ደካማው ሲበረታ የበላዩ የበታች የበታቹ የበላይ ሲሆን በዓለም ላይ ኖሯል ብዙ ጊዜ የአሸናፊነትን አርማ ጨብጠው ነፃነታቸውን ሳያስነጥቁ የምናገኛቸው እግዚአብሔርን ረዳት አድርገው የተነሡ ሕዝቦች ብቻ ናቸው በተለይ በዘመነ መሳፍንት በእስራኤላውያንና በምድያማውያን መካከል አለመግባባት ስለነበር ለጦርነት ቦዝነው አያውቁም ነበር ፣ በዚያን ጊዜ ምድያማውያን በኃይል በርትተው አለን ፣ አለን ይሉ ስለነበር በዘር ወራት ወደ እስራኤላውያን መሬት ሠርገው በመግባት የበቀለውን አብልተውባቸው ፣ ያልበቀለውን አስጠቅጥቀውባቸው ይሄዱ ነበር ፣ ይህ ብቻ አይደለም፤ በመከርም ወራት ሾልከው ወደምድራቸው ገብተው የሸተውን ለከብት አብልተውባቸው የደረቀውን በእሳት አቃጥለውባቸው ይመለሱ ነበር፡— ይህንን የመሰለ ጥቃት በእስራኤላውያን ላይ ተደጋግሞ ሲደርስባቸው ከዚህ መጥፎ አድራጐታቸው እንዲቆጠቡ ፣ ለምድያማውያን ተነግሯቸው ነበር ፣ እነርሱ ግን ሊታገሡ አልቻሉም እንዲያውም የሚፈጽሙትን ተግባር እያደር እያጠነከሩት ይሄዱ ጀመር ።

ከብዙ ትዕግሥት በኋላ እስራኤላውያን ከመካከላቸው አንድ ለሀገርና ለወገኑ ፣ ፍቅር ያለው የጦር መሪ መረጡና ጠላቶቻቸውን ለመዋጋት መዘጋጀት ጀመሩ በዚያን ጊዜ ከእነርሱ ወገን በፈቃደኝነት ለመዝመት የተመዘገቡት ሰዎች ቁጥር ከ32.000 በላይ ሆኖ ነበር ፣ ግን የተመዘገቡት ሁሉ ወደ ጦር ግንባር እንዲሄዱ አልተደረገም ፣ ልዩ ልዩ ችግርና ምክንያት ያለባቸው በሀገር ቤት ሆነው የሚፈለግባቸውን ሥራ በትጋትና በንቃት እንዲያከናውኑት ተደረገ፡እነዚያ ለጦርነት የተመደቡት ሠራዊቶች ለጦር መሪነት ከተመረጠው ጌዴዎን ከተባለው ጀግና ጋር ሆነው ወደጦሩ ሜዳ ጉዟቸውን ቀጠሉ ለጦርነቱ የተመረጡት ሠራዊቶች ልበ ሙሉዎች ጀግኖች ከመሆናቸውም ሌላ ለሥጋዊ ሕይወታቸው ፈጽመው የማይመለሱ ፣ ሀገራቸውን ከጠላት እጅ ለሁል ጊዜ ነፃ ለማውጣት ከሕዝብ እምነት የተጣለባቸው ነበሩ ።

በዚያን ጊዜ ሠራዊቱ ወደጦርነቱ ሲሄዱ ይዘውት የዘመቱት የጦር መሣሪያ ብቻ አልነበረም ከጦር መሣሪያቸው ጋር ይዘውት የነበረው መፈክር “ኃይል የእግዚአብሔር ጦር የጌዴዎን” የሚል መፈክር ነበር ሠራዊቱ ይህንን መፈክር ይዘው ባላቸው የጀግንነት ወኔ በመዋጋታቸው ጠላቶቻቸውን አጥፍተው የሀገራቸውን ዳር ድንበር አስከብረው ተመልሰዋል ።

ከዚያ በኋላ እስራኤላውያን ወደ ጦር መሪው ወደ ጌዴዎን ሄደው “ከጠላቶቻችን ከምድያማውያን ነፃ አድርገኸናልና አንተ ልጅህም ፣ የልጅህም ልጅ ግዙን አሉት ፣ ጌዴዎንም መለሰ እኔ አልገዛችሁም ልጄም አይገዛችሁም የልጅ ልጄም አይገዛችሁም እግዚአብሔር ይገዛችኋል ሲል ይህ ታላቅ ጀግና ኃይሉንም ድሉንም ያቀዳጀው እግዚአብሔር መሆኑን በሕዝቡ ፊት መሰከረ ፣ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስራኤላውያን ጠላቶቻቸው ጠፍተውላቸው 40 ዘመን ሙሉ ያለ ምንም ሥጋት በሰላምና በጤና ለመኖር በቅተዋል ። (መሳፍንት 7 - 25 - 8 - 28)

ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር ያልተባበረ ጀግንነት ጥንካሬ ሊኖረው አለመቻሉን ፣ ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር ተዋህዶ ያለው ኃይል ደግሞ ማንም ኃይለኛ ፣ ማንም ዕብሪተኛ ማንም ትዕቢተኛ ድል ሊያደርገው አለመቻሉን ከዚህ ከተጠቀሰው ታሪክ ለመረዳት ይቻላል ። ስለዚህ ለጦርነት ዝግጅት ሲደረግ አብረው ሊታሰቡ የሚገባቸው ሁለት ነገሮች ናቸው ፣ እነዚህም አንደኛ በእግዚአብሔር ኃይል መታመን ሁለተኛ ቆራጥነት ናቸው እነዚህን አሟልተው ይዘው ጠላትን ለማጥቃት የተሰለፉ ሠራዊቶች ሁሉ ከጠላት ተቃውሞ ግንባራቸውን አያጥፉም የማሸነፍ እንጅ የመሸነፍ ዕድል በፍጹም አይደርስባቸውም ፣ ትምክህተኛውንና ዕብሪተኛውን በመሣሪያውና በጉልበቱ ተመክቶ የተነሣውን ጠላት ከመደምሰስ ወደ ኋላ አይሉም ይህም አዲስ ሳይሆን ተደጋግሞ የተፈጸመ መሆኑን ታሪክ ይመሰክራል ።

ሩቅ ሳንሄድ ሀገራችን ኢትዮጵያም ጠላቶቿን እያጠቃች ዳር ድንበሯንአስከብራ የኖረችው በጦር መሣሪያ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር ባላት የመንፈስ ግንኙነት መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም የጦር ሠራዊቱ ወደ ጦር ግንባር ሲገሠግሡ ቤተክርስቲያንም በበኩሏ ስለሀገር ነፃነትና አንድነት ስለሰላምና ስለፍቅር ስለ ሠራዊቱ ኃይልና ብርታት ወደ ፈጣሪዋ ትጸልያለች በዚህም ጠላቶቿን ድል ስትመታ ኑራለች አሁንም ወደፊትም ቤተ ክርስቲያን ጠላቶቿን የምታጠቃው በግዙፍ የጦር መሣሪያ ብቻ ሳይሆን ወግቶ ሲጥል በማይታይ የመንፈስ መሣሪያ ጭምር ነው ።

በተለይ በአሁኑ ወቅት ሀገራችን በጠላት ኃይል መከበቧን የማያውቅ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝም ፣ ቤተ ክርስቲያንም በሰላም ጊዜ ወንጌልን በጦርነት ጊዜ ደግሞ ወኔን የሚቀሰቅስ ትምህርት ለሕዝብ የማስተማር ኃላፊነት አለባት ጠላት ዙሪያውን አፉን ከፍቶ ሀገራችንን ለመዋጥ በሚስገበገብበት በአሁኑ ጊዜ ቤተ ክርስቲያናችን ፊቷን ዘወር ብላ አፏን ዘግታ በገለልተኛነት ለመመልከት አትሻም ፣ ንቅታና ተግታ ሕዝቡን በሞራል የመቀስቀስ ግዴታ እንዳለባት ትገነዘባለች በሀገር ላይ ችግርና መከራ ሲደርስ የመጀመሪያውን የመከራ ጽዋ የምትጨልጠው ቤተ ክርስቲያን መሆኗዋ የቆየው ታሪክ በቂ ምስክር ነው ፣ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያናችን በተቻላት መጠን ኃይለ እግዚአብሔርን የተመረኮዘ የሞራል ትምህርትን አስፋፍታ ለሕዝብ ማስተማር ያለባት በአሁኑ ጊዜ ይመስለኛል እኛን ለማጥፋትና ሀገራችን ለመንጠቅ ለተሰለፈው ጠላታችን የሚደረግለት የመሣሪያና የገንዘብ ፣ የወታደርና የማቴሪያል ዕርዳታ ሁሉ እምነትን የተደገፈ መሆኑ ይነገራል ፣ ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያናችን የሚካሄደው ጦርነት ሁሉ ሀገርን ና እምነትን ጭምር የሚነካ መሆኑን አውቃ በጥንቃቄ ፣ ከማስተማር ወደ ኋላ አትልም ።

ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ሀገር የሁሉም ኢትዮጵያዊ መሆኑን እናውቃለን ፣ በአንድ ሀገር ደግሞ ብዙ የሃይማኖት ድርጅቶች የመኖር ነፃነት ያላቸው መሆኑን አንክድም ይህ ሆኖ ሳለ የሀገ


www.ethiopianorthodox.org

ራችንን አንድነት ለመከፋፈል ሲሉ ጠላቶቻችን የሚያደርጉትን የተንኰል ሙከራ ቤተ ክርስቲያን በገለልተኛነት አትመለከትም ።

ሰይጣን ሰውን የሚፈታተነው በልዩ ልዩ መንገድ ነው በይበልጥ ደግሞ የሰይጣን ፈተና በሰው ላይ የሚበረታውና የሚጠነክረው አንድ ሰው አንድ ጠቃሚ ነገር ጀምሮ ወደ መጨረሻው ግብ ለመድረስ በተቃረበ ጊዜ መሆኑ የተረጋገጠ ነው ። ይህንንም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፈተና ለመረዳት እንችላለን ክርስቶስ ወደ ገዳም ሂዶ 40 ቀንና 40 ሌሊት እስከሚጾም ድረስ ሰይጣን አልተፈታተነውም ነበር የተፈታተነው ከ40 ቀን በኋላ ወደ መጨረሻው ግብ ሲደርስ ነው ማቴ 4፥1

በዚህ አንጻር ስንመለከት አሁን በሀገራችን ላይ የተነሡት ጠላቶች እስከ ዛሬ ድረስ ነበሩ ፡ ግን እንዳአሁኑ ባለ

አሁኑ ጠላቶቻችን ከመቼውም በበለጠ ዙሪያውን አስፍስፈው ተነሥተው ብናል ይህም የሚያመለክተን የተደረገው ለውጥ ወደ ጠቃሚ ነገር መቃረቡን

ነው ቢሆንም ዛሬም ፡ ነገም ከነገ ወዲያም የተነሡብንና የሚነሡብንን ጠላቶቻችን "ኃይል የእግዚአብሔር ጦር ሰፈው ሕዝብ" የሚለውን መፈክር በመያዝ ድል እናደርጋቸዋለን ፡ ይህንን አርማ ይዘን ከተሰለፍን እግዚአብሔር አምላካችን በግንባር ቀደምትነት አብሮን እንደሚሰለፍ እናምናለን እርሱ አብሮን ከተሰለፈ ደግሞ ድሉ የእኛ መሆኑ አይጠራጥርም ።

መዝሙረኛው ዳዊት "በአንተ ጠላቶቻችን እንዋጋቸዋለን ፡ በስምህም በላያችን የቆሙትን እናዋርዳቸዋለን" ብሎ ተናግሯል መዝ. 43፥ 5 በዕርግጥ ከጀግንነትና ከቆራጥነት ጋር ኃይለ እግዚአብሔር እንዲኖር ያስፈልጋል ፡ ይህ ከሆን በእግዚአብሔር ስም ጠላቶቻችን እንደመስሳቸዋለን ኃይለ እግዚአብሔር ባልተለየው ክንዳችን የጠላቶቻችን ኃይል እንሰብረዋለን እኛን ለማዋረድ የተሰለፉትን እናዋርዳቸዋለን ከምድራችንም ጠራርገን ድርሻቸውን እናጠፋዋለን ።

ዕብራተኛውን ጠላት ጐልያድን መዝሙረኛው ዳዊት የገደለው መሣሪያ መርጦ በመያዝ አልነበረም የገደለው ከወንዝ ዳር በለቀመው ድንጋይ በመወንጨፍ ነበር ስለዚህም ራሱ ሲመሰክር "እኔም ድንጋዮችን አነሣሁና ወንጭፌ የጐልያድን ግንባር መታሁት ያንጊዜም በእግዚአብሔር ኃይል ወደቀ በላዩ ያለውን ሰይፍም አንስቼ ያዝሁ የጐልያድንም ራሱን ቆረጥሁ ከእስራኤልም ልጆች ስድብን አራቅሁ ብሏል (መዝ.151፥7፥8)። ይህ ጐልያድ የተባለው ሰው ዕብራተኛ ከመሆኑ የተነሣ ማንም አያሸንፈኝም እያለ የእስራኤልን ሕዝብ ለሰባት ቀናት ያህል ሲዘልፍና ሲገደል ከቆየ በኋላ ከአንድ በግ እረኛ በተወነጨፈ ድንጋይ ሕይወቱ እንደጠፋ ተገልጿል ።

እንደዚሁም ዓለምን በሙሉ እንደ ሰም አቅልጠን እንደ ገል ቀጥቅጠን እንገዛለን ብለው በተንኮልና በዕብሪት ተነሥተው የነበሩት ሂትለርና ሞሶሎኒያ ርኩስ ዓላማቸው ከግብ ሳይደርስላቸው ከንቱ ቀርተዋል በተንኮል ተነሣሥተው የፈጸሙትን መጥፎ ተግባር ዓለም በጥቁር ቀለም መዝግቦ ይዞ ለክፉ ሥራ ማስረጃ በማድረግ ሲጠቀምበት ይኖራል ። ይህም የሚያስረዳው የክፉ ሰው ዓላማው ግቡን የማይመታና አወዳደቁም እጅግ በጣም የከፋ እንደሚሆን ነው ።

የሀገር ጉዳይ ወንድ ሴት ትልቅ ትንሽ ደካማ ጠንካራ ወጣት ሽማግሌ የሚያሰኝ አይደለም ፡ ጠላት ከመጣ ምርጫ አያደርግምና እንዲያውም ፡ መከራው የሚጸናው በደካሞች በሽማግሌዎችና በወጣቶች መሆኑ አይጠራጠርም ። ስለዚህ ሁሉም ሰው ለሀገሩ ለወገኑ የሚያበረክተው ድርሻ ይኖረዋል ከዚህ ላይ ሶምሶን የተባለውን ሃገር ወዳጅ ጀግና ላስታውስ እፈልጋለሁ ፡ ይህ ጀግና ለጠላቶቹ የማይበገር በተሰለፈበት ሁሉ ጠላቶቹን የሚደመስስ ነበር ፡ ጠላቶቹንም የሚበቀላቸው የጦር መሣሪያ መርጦ በመያዝ ሳይሆን በማንኛውም መሣሪያ ነበር ። ሌላው ቀርቶ ጠላቶቹን በአጥንት ወርውሮ እንደደመሰሳቸው ከታሪክ እንረዳለን ።

ይህንን ጀግና ጠላቶቹ በጣም ይፈ



በሸዋ ክፍለ ሀገር በመንዝና ግሼ አውራጃ በመሐል ሜዳ ከተማ በልዩ ልዩ እጎት አብያተ ክርስቲያናት እርዳታ አዲስ የተሠራው የደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከአንድ ዓመት በፊት በዚህ ደረጃ ላይ ነበር። በደማቅ ሁኔታ ቅዳሴ ቤቱ ተከ አሁን ግን የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ተፈጸሞ ኅዳር 12 ቀን 1970 ዓ.ም. ብሮ ውሏል ።

ይህ ቤተክርስቲያን በተጨማሪ የካህናት ማሠልጠኛ ት ቤትና የሰንበት ትምህርት መስሜ የስብሰባ አዳራሽ ፡ እንዲሁም የዕቃ ግምጃ ቤት ፡ የክርስትና ማንሻና የሰበካ ጉባኤ ጽ ቤት የተሠራበት ስለሆነ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሙሉ ድርጅት እንደሚኖረው ታውቋል ።



# ትንሣኤ ዘጉባኤ ያተመው አዲስ መጽሐፍ

ሽፍት ሰውነት

ከደነተው አማዩ ፡

ገጽ ................................................ 187

ዋጋ ................................................$2.60

አሳታሚ ትንሣኤ የማሳተሚያ ድርጅት

ፖ.ሣ.ቁ. 31240 ፡ ስልክ ቁ. 124261 አ.አ.

ሽፍት ሰውነት ፡ ልብ ወለድ ሲሆን የሚተርከው ንጉሡ ጥሩነህ ስለተባለ የተማረ ሰው ነው ንጉሡ በልጅነቱ ፡ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ በጐጃም ክፍለ ሀገር ትምህርቱን ያጠናቅቃል ፡ በኋላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትምህርቱን ይጨርስና አሜሪካን ሀገር ድረስ ሂዶ ትምህርቱን ጨርሶ ይመለስና በአንድ ኩባንያ ውስጥ በ$975 ብር ተቀጥሮ ይሠራል ።

ንጉሡ ከመጀመሪያ ጀምሮ ከፍተኛ ትምህርት አጠናቆ በሥራ ላይ እስከዋለ ድረስ እንዲሁም በሥራም ላይ እያለም (ኋላ ሊገለጥበት) በጣም ለሕዝብ አሳቢ መስሎ ለመታየት ይሞክራል ፡ ዘመዶቹ ንጉሡን ለማስተማር በግ እስከመሸጥ ደርሰዋል ። ሀገሬቱም ከአንደኛ ደረጃ እስከዩኒቨርሲቲና ቀጥሎም የነፃ ትምህርት በመስጠት ከፍተኛ ወጭ አድርጋ አስተምረዋለች ፡ ሆኖም ንጉሡ ዘመዶቹን በሚያገኘው ሀብት ፡ ሀገሩንም በቀሰመው ዕውቀት ሊረዳ ፈቃደኛ ሆኖ አይታይም ፡ እንዲያውም ሀገሩንም ሆነ ወገኖቹን ያታልላል ፡ የልጅነት ወዳጁን አገባሻለሁ ሲል ቆይቶ ዩኒቨርሲቲ ሲገባ ሌላ ሲያገኝ ይተዋታል ፡ የዩኒቨርሲቲ ተማሪ ሆኖ አንዲት የቤትኛ አዳሪ እንድትወደው ያደርግና የስፈት መኪና ገዝቼልሽ ትነግጃለሽ ፡ ባልም ታገቢያለሽ ብሎ በስንት ችግር ያጠራቀመችውን $600 ብር ወስዶባት ይጠፋል ፡ ሌላዋንም አሜሪካን በሚቆይበት ጊዜ አግኝቷት አገባሻለሁ ቢላትም በመጨረሻ ማንነቱን የንጉሡ ታናሽ ወንድም ዋጋዬ ከጻፈው አንብባ ካልጨረሰችው የወቀሳ ደብዳቤ ስለምትረዳ "ስማህ ንጉሡ የመወዳጀ መልካም ምግባር ስለሌለህ አዝናለሁ...የሞላልህ ባለፀጋ ፡በንጹሕ ድሀዎች ወዝ የበለፀግህ መሆንህ ይሰማኛል...ለወገኖችህ ያልሆንክ ለኔ መሆንህ ያጠራጥራል...የወንድምህን ደብዳቤ ባልቀደድከው ኖሮ ስንት ነገር ቢኖር መንታ አርግዤ በነፃ እንድትሄድ መፍቀዴ ነው ፡ ... አንተ ልስን መቃብር ነህ ፡ ውስጥህ የበከተ የተበላሸ" ትልና በሩን የኋሊት ዘግታበት ትለየዋለች ።

ደራሲው እንዳንድ ለመማር ዕድል ያገኙ ኢትዮጵያውያን በትምህርታቸው ሀገራቸውንና ወገኖቻቸውን በማገልገል ፋንታ የግል ፍላጐታቸውን ብቻ የሚያሳድዱ መሆናቸውን ይገልጻል ። ንጉሡ በወር $975 ብር እያገኘ ወላጆቹ በረሃብና በችግር ተሰቃይተው በመጨረሻም የአባቱን ሞት ቢሰማም ፡ ታናሽ እህቱም በችግር ምክንያት ትምህርቷን አቋርጣ ሴትኛ አዳሪ መሆኗን ቢያውቅም ፡ "የት ወደቃችሁ" አይላቸውም ፡ በሥራም ሰዓት ሥራውን ጥሎ ወደ ቤቱ ይመለስና በመጨረሻ ምንነቱን ስታውቅ ጥላው ከምትሄደው ዕጮኛው ጋር ሲዳራ ይውላል ። እያንዳንዱ የተማረ ኢትዮጵያዊ እራሱን ከሽፍት ሰውነት ሚዛን ላይ አስቀምጦ እራስ ወዳዱንና ምግባረ ቢሱን ንጉሡ ጥሩነህን ወይም በታሪኩ ውስጥ ለሀገርና ለወገን ተቆርቋሪና አሳቢ የሆነውን መሠረትን መሆኑን እንዲያመዛዝን ይረዳዋል ።

ታሪኩ በኅብረተሰባችን ውስጥ ያለውን ዝብርቅርቅ ሁኔታ ፡ በአዲሱ ባህልና ባሮጌ ባህል መካከል ያለውን ቅራኔ የሚገልጽ ከመሆኑም ሌላ በቀላልና በጣፋጭ አማርኛ ስለተጻፈ ማናቸውም ሰው መጽሐፉን አንብቦ ይደሰትበታል

# ኃይል የእግዚአብሔር ....

ሩት ስለነበር ፊት ለፊት ተጋጥመው የማያቸንፉት መሆናቸውን ተረዳና ለማጥቃት የተሻለ መስሎ የታያቸው በገዛ ወገኖቹ አማካይነት ይዘው ማስቃየት ነበር ። ስለዚህ በገዛ ወገኖቹ ተባባሪነት ይዘው ማርከው ወደ ሀገራቸው ከወሰዱት በኋላ ሁለት ዓይኖቹን በፍላት አጥፍተው መሳቂያና መሣለቂያ አደረጉት ጀግናው ሶምሶን ልዩ ልዩ ሥቃይ ቢደርስበትም የሀገሩና የወገኑ ፍቅር ከልቡናው ፈጽሞ ሊፋቅ አልቻለም፡ ጠላቶቹ በሀገሩና በወገኖቹ ላይ የሚፈጽሙትን በደልና ግፍ በጆሮው እየሰማ በጣም ይናደድ ነበር ፡ ከዕለታት አንድ ቀን ጠላቶቹ በአንድ ሰፊ አዳራሽ ውስጥ ተሰብስበው ሲጫወቱ ለመቀለድ ያመቻቸው ዘንድ ሶምሶንን አስመጥተው ይቀልዱበት ጀመር ሶምሶን ግን ሁሉንም በአንድነት ለመበቀል የሚቻልበት አጋጣሚ ሆኖ ስላገኘው የአዳራሹን ምሰሶ እንዲያስይዘው አንድ ሰውለምኖ ካስያዘው በኋላ "አንድ ጊዜ ብቻ አበርታኝ" ብሎ የእግዚአብሔርን ስም በመጥራትና ከጠላቶቹ ከኢሎፍላውያን ጋር ነፍሴ ትውጣ ብሎ ምሶሶውን ቢወዘውዘው አዳራሱ ተገልብጦ በውስጡ የነበሩት 3000 ሰዎች ሲያልቁ እርሱም ከጠላቶቹ ጋር ሕይወቱ አልፏል መሳፍንት 16 ፡ 28 - 31

ጀግና ምን ጊዜም ጀግና ነው በመከራም ሆነ በችግር ፥ በበሽታም ሆነ በእርጅና የጀግንነት ጠባይ ምን ጊዜም አይለወጥም የሚኖረው ከደም ጋር ተዋህዶ ነውና ጀግንነትን ገንዘብ ያደረገ ሰው ከራሱ ሕይወት ይልቅ የሚያስበውና የሚቆረቆረው ለሀገሩና ለወገኑ ነፃነትን ነው ፡ ከወራዳ ኑሮ የሚመርጠው ሞትን ነው ደካማም ቢሆን እንደ ሶምሶን የሞራል ጥንካሬ ካለው ለሀገሩና ለወገኑ የሚያበረክተው የተቀደሰ ታሪክ ይኖረዋል ፡ እንዲሁም ወደ ጠማቶች እንመልከት ከላይ እንደተጠቀሰው ዕብሪተኛውን ጠላት ጐልያድን በድንጋይ ልብራሱን ብሎ የገደለው የበጐች ጠባቂ የነበረው ወጣቱ ዳዊት ነው ። ይህንንና የመሳሰሉትን ታሪኮች ስንመለከት በሀገር ላይ የመጣውን ጠላት ለመደምሰስ የሚፈለገው ዘመናዊ መሣሪያ ብቻ አይመስለንም ፡ ወይም የሰለጠነ የሰው ጉልበት ብቻም አይሆንም ጠላትን ለማጥቃት የሚያስፈልጉ አንደኛ የእግዚአብሔር ኃይል ፡ ሁለተኛ የሀገርና የወገን ፍቅር ከመሣሪያ ጋር ናቸው ።

እንግዲህ በተንኮልና በዕብሪት የተነሡብንን ጠላቶች ለማጥቃት ዛሬም ነገም ፡ ከነገ ወዲያም ሳንል "ኃይል የእግዚአብሔር ጦር የሰፈው ሕዝብ" ነው የሚለውን ቃለ መፈክር የመያዝ ግዴታ ይኖርብናል ፥ ይህንን መፈክር ይዘን ከተሰለፍን ጠላቶቻችን እናሸንፋቸዋለን "ኃይል የእግዚአብሔር ጦር የብዙኃን ሕዝብ ነውና ፡

ቄስ ልሳኑ በዛብህ



www.ethiopianorthodox.org

# የክርስቲያናውያት ሴቶች ድርሻ በቤተክርስቲያን

ሁላችንም እንደምናውቀው በማንኛውም አብያተ ክርስቲያናት ቢሆን ሁኔታው የተለያየ ይሁን እንጂ ባጠቃላይ ሲታይ የሴቶች መንፈሳዊ አገልግሎት እጅግ በጣም የተወሰነ እና ዝቅ ያለ ነው ። እንዲያውም በአንዳንድ አብያተክርስቲያናት ሴቶች ከነአካቴው በምንም ዓይነት መንገድ የመንፈሳዊ አገልግሎት ድርሻ ስለሌላቸው ሴቶች ተከታዮች ፣ ሰሚዎች ባጠቃላይ ተገልጋዮች ብቻ ስለሆኑ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሥራፈቶች ወይም ባይታወር ሆነው ሲመላለሱ እንመለከታለን ።

ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለ አንደኛ ሴቶችን እንደ ዕቃ ብቻ አድርጎ የሚቆጥረው ባህላችን ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ይኸው ባሕል በሃይማኖት ሰበብ በወንዶችም ሆነ በሴቶች አእምሮ ያሳደረው የአስተሳሰብ ተጽዕኖ ባስከተለው መዘዝ እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው ። ስለሆነም ሴቶች በማኅበራዊ ኑሮ በኩል ባላቸው አቋም ብቻ ሳይሆን በአገልግሎትም በእኩልነት ደረጃ ባለመሆኑ በቤተክርስቲያን ያላቸው የአገልግሎት ድርሻ በጣም የተወሰነና የመነመነ ነው ።


ሆኖም ሴትና ወንድ ሁለቱም በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩ ከመሆናቸውም በላይ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በተገኘው የደኅንነት ፀጋ የሁለቱም አቋም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እኩል እንደሆነ በገላትያ 3 ፡ 28 ተጽፎ እናገኛለን ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የኦሪትን ቀንበር በመስቀሉ ሰብሮ ፍጹም የሆነውን ነፃነት ለሰው ልጆች ሁሉ ሰጥቶአል በዮሐንስ ወንጌል 1 ፡ 12 ደግሞ "በስሙ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው ።" ተብሎ ተጽፎአል ። እንግዲህ ክርስቲያናውያት ሴቶችም የልጅነት መብትና ግዴታ እንዳላቸው ለመገንዘብ አያዳግትም ።

በተጨማሪ በ1ኛ ጴጥሮስ 2 ፡ 9 እና 4 ፡ 10 እንደምንመለከተው በክርስቶስ ያመነ ሁሉ የእርሱን (የክርስቶስን) በጐነት ወይም የማዳን ኃይሉን እንዲናገር (እንዲሰብክ) እንዲመሰክር የተመረጠ ትውልድ ፣ ቅዱስ ሕዝብ ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ፣ ብቻ ሳይሆን የክርስቶስ ካህን እንደሆነ ስናነብ እያንዳንዱ አማኝ የክህነት መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም እንዳለበት በግልጽ እንረዳለን ይህም ማለት የክርስቶስን ወንጌል የሚሰብኩት ለክህነት አገልግሎት ልዩ የእግዚአብሔር ጥሪ ደርሶአቸው ለሥራው የተለዩት ብቻ ሳይሆኑ እያንዳንዱ ክርስቲያን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንዳለው ሲያመለክት ነው ። ይኸው መብትና ግዴታ ሴት ወንድ ሳይለይ "የማዳን ኃይሉን ለተመሰ ሁሉ" የተሰጠነው ። በማቴዎስ ወንጌል 25 ፡ 14-15 ደግሞ እያንዳንዱ ክርስቲያን የአገልግሎት መክሊት እንደተሰጠውና በመክሊቱ ደግሞ ሠርቶ የማትረፍ ግዴታ እንዳለበት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተምረናል ። እንግዲህ ሴቶችም ያገልግሎት መክሊት እንደመስጠታቸው መጠን ሰርተው ለማትረፍ እንዲችሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ባላቸው የመክሊት ዓይነት እንዲያገለግሉ ግዴታ ስላለባቸው የአገልግሎታቸውን ድርሻ ለመወሰን ሥልጣን ያለው መክሊቱን የሰጣቸው ብቻ ነው ።

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በተለይ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12 ፡ 4 እንደምናነበው በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የተለያዩ የአገልግሎት ዓይነቶች እንዳሉ ስንመለከት ስጦታውም ለያንዳንዱ አማኝ የሚሰጠው እሱ እንደፈለገ ወይም እንደ እውቀቱ መጠንና እንደስሜቱ ወይንም ሌሎች የቤተክርስቲያን ሰዎች በሚወስኑት ውሳኔ ሳይሆን እንደ መንፈስ ቅዱስ እንደፈቀደ ብቻ ለያንዳንዱ ምዕመን እንደሚያካፍል በግልጽ እናያለን ። እንግዲህ እያንዳንዱ ክርስቲያን የደኅንነት ፣ ፀጋ እንደተቀበለ መጠን የአገልግሎት ኃላፊነትም የተሰጠው ከሆነ የአገልግሎቱን ዓይነት መንፈስ ቅዱስ ብቻ እንደፈቀደ የሚሰጠው ከሆነ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሴቶችን የአገልግሎት ድርሻ መወሰኑ ስሕተት መሆኑን በግልጽ እንገነዘባለን ።

እስካሁን በተጠቀሱት ጥቅሶች መሠረት እንደተመለከተው ሴቶች የክርስቶስ የደህንነቱን ፀጋ በሙላት እንደመቀበላቸው መጠን ለአገልግሎትም ሙሉ መብት ብቻ ሳይሆን ግዴታም እንዳለባቸው እንጂ የአገልግሎት ገደብ እንደተሰጣቸው አንመለከትም ። ስለሆነም እያንዳንዷ ክርስቲያናዊት ሴት እሷ በምትፈልገው ወይም ሰዎች በሚወስኑላት ውሳኔ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስ የሰጣትን የአገልግሎት ስጦታ ምን እንደሆነ እንዲገለጽላት በጸሎትና በጾም በእግዚአብሔር ፊት በመቅረብ ስጦታውን ማወቅ ይገባታል ። ካወቀችም በኋላ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እሱ በወሰነላት ቦታ ሆና እንድታገለግል የቤተክርስቲያን መሪዎች ሊያደፋፍሯትና ሊያግዟት እንጂ እንቅፋት እንዳይሆኑባት በተለምዶ የተሳሳተ አስተሳሰብ ሳይሆኑ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሊሆኑ ይገባቸዋል ።

ወ ት ጸገ ወንጌል ተክለ አብ



በመሠራት ላይ ያለው የጉለሌ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል አዲሱ ቤ/ክርስቲያን

ለክ ________________

መገፈግሮ መላምታችንን በትድሚያ እናቀርባለን

የጉለሌ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን በዘመናዊ ፕላን ለማሠራት ሥራው ተጀምሮ በመካሄድ ላይ መሆኑ ይታወቃል ። ሥራውንም ለማጠናቀቅ $700,000 ብር እንደሚፈጅ በመሃንዲሶች ተገምቷል ። ________________

ድርጅቱ በአሁኑ ወቅት ይህን ያህል ገንዘብ የሌለው በመሆኑ ሥራው የተጀመረው የቤተ እግዚአብሔር ፍቅር ያለው ሕዝበ ክርስቲያን መዋጮውን በመተማመን ነው ።

ስለዚህ እርስዎም ለዚሁ ቤተ ክርስቲያን ግሠራያ አስተዋጽዖ ማድረግ ክርስቲያናዊ ግዴታዎ ስለሆነ የተቻለዎትን ያህል ይለግሱ ዘንድ ኮሚቴው በትህትና ይጠይቃል ። ________________



# ከእናት ትሻሌ ሞግዚት

"የሞኝ ምስጋና ፡ የግንቦት ደመና" የሚል ምሳሌያዊ የአነጋገር ዘይቤ አለ ። ጥቅምት 6 ቀን 1970 ዓ.ም. "የትንሣኤ መጽሔት በስህተት ላይ ስሕተት" በሚል ርእስ በዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ መምህር ሀብተ ማርያም ተድላ አውተርትረው ያቀረቡት ጽሑፍ የመቅድመ አሳቡ ውዳሴ ከዘለፋ ትችት ጋር ሲታይ ይህኑ ይመስላል ።

"እንደ ቆጫት ተነሥታ የሰው ለቅሶ አበላሸች" እንዲሉ እኚህ መምህር መሳይ ጸሐፊ (ጋዜጠኛ) የትንሣኤ መጽሔት ብዙ ጊዜ የተደጋገመ ስህተት የሚጽፍ በማስመሰል ቅንጣት ሐቅ በሌለው ምክንያተ ነገር የትችት ብርዕ በመምዘዝ ያለስሙ ስም ሊሰጡት ሞክረዋል። ትችቱንም ያቀረቡት ለቤተክርስቲያን ፍጹም ተቆርቋሪነት ያላቸው መምህር ወመገሥጽ ዘኢያደሉ ለገጽ መስለው የአዞ ዕንባ እያፈሰሱ ስለሆነ ምናልባት አንድ አንድ የርሳቸውን መሰል አሳበ ውሱን አንባቢዎች ያስበረግግ ይሆናል ብለን በመገመት ብቻ አጭር መልስ ልንሰጥበት ተገደድን ።

አወ "መርፌ መግቢያዋን እንጂ ዞራ መውጫዋን አታይም" ይባላል ። ይህም ለወጉ ያህል እንጂ መርፌስ ከነጭሩ መግቢያዋንም የማታይ ግዕዝት ናት ። የእኛም ሐስ አቅራቢ መምህር ዘለው ከገቡበት የትችት ማጥ በየት በኩል መውጣት እንደሚችሉ ግራና ቀኝ መለስ ቀለስ ብለው መልካውን የቃኙት አይመስሉም ።

በዕርግጥ እኚህ ሐስ ፈልፋይ መምህር ምድብ ደረጃቸው ከሊቃውንት ወገን መሆኑ ይነገራል ። ያለጥርጥር የሊቃውንት ጉባኤ አባል መሆናቸውን ከሰማን ውሎ አድሮአል ። ዳሩ ግን ለዚህ ጉባኤ አባልነት ያበቃቸው የሊቅነት መለኪያ ምን ነበር? መልሱን ለደረጃ መዳቢው ጉባኤ ሊቃውንት እንተዋለን ። ያም ሆነ ይህ የሊቃውንት ጉባኤ አባልነቱን ስም በችሎታም ይሁን ወይም ባጋጣሚ ተሸልመውታልና ይቅርባቸው እንልም የምናቀርብላቸው ምክር ቢኖር ይህን ታላቅ ማዕርግ አስከብረው በጥንቃቄ እንዲይዙት ብቻ ነው። ሌላው ቢቀር አሁን ያሉበት አማካይ የሽምግልና ዘመን እንኳ ከእንዲህ ዓይነቱ ተራ ስህተት እንዲታረሙ ብዙ ጥበብ ሊያስተምራቸው ሲገባ እንዴት በዚህ ዓይነት ውጥን በጅምር ተዋቸው? ተብሎ ቢጠየቅ ማጣፊያው ያጥራል ። አሁንም ጊዜ ይፍታው ዘመን ይምከራቸው ዕድሜ ያስተምራቸው ብሎ ዝም ማለቱ በቅዱስ መጽሐፋችንም የሚያስወቅስ በመሆኑ የማያዳግም ትምህርትና ተግሣጽ መስጠት ክርስቲያናዊ ግዴታ ሆኖ አግኝተዋል ።

ለዚህም ፍሬ ነገሩን ከሥሩ ማምጣት ይጠቅማል ። ይኸውም ባለፈው መስከረም ወር 1970 የሁለት ግለሰቦች አስተያየት አዘል ጽሑፎች በትንሣኤ መጽሔት ታትመው መውጣታቸው ይታወሳል ። አንዱ ጽሑፍ "ሃይማኖት አይለያየንም" በሚል ርእስ ከመምህር ኪዳነ ማርያም የቀረበ የመጽሐፍ ማስተዋወቂያ ሲሆን ስለ መጽሐፉ ጠቃሚነትና ጉጂነት መጽሔቱ የሰጠው ማብራሪያ የለም ኃላፊነቱንም ወስዶ ያሳተመው እርስዎ ያሉበት የትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ነው ። ሌላው "ሴቶች በሃይማኖት" በሚል ርእስ ወ/ት ታሪኳ ምስክር ከተባለች ወጣት የተቀነባበረ ዘመናዊ ድርሰት ነው ። ታዲያ ሊቁ ይህን ሲመለከቱ ደማቸው የፈላበት ምክንያት ምን እንደነበርና ለምን እንደተነሣሡም ምሥጢሩ ግልጥ አይደለም ። ጸሐፊዋ ያላሰቡትን ትርጉም እኚህ ሊቁ እንደሰን በሌጥ በመሰባበር የትችት ናዳ ሲሰዱ እግረ መንገዳቸውን የትንሣኤን መጽሔት አሸሚጠውታል ።

በጣም የሚያሳዝነውና ሊቅነታቸውንም ሊያስገምት የቻለው በግለሰብዋ ጽሑፍ ለአምልኮ ጣዖት የተሰጠውን ታሪክ ከዕውነተኛው የቤተ መቅደስ ታሪክ ጋር አዛምደው ያለመልኩ የተዘበራረቀ ጉራማይሌ ትርጉም ሊያስተምሩን መሞከራቸው ነው ። በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ ደንጊያ ሁለት ብቻ ሳይሆን 3 ወፍ ለመግደል አስበው በመጽሔቱ ላይ ሐቀኛነት የጐደለው ሐስ ለመሠንዘር መሞከራቸው ለምን ይሆን?

በመሠረቱ ይህ መጽሔት በርከት ላሉ ዓመታት መታተሙ ተቋርጦ ቆይቶ ከ4 ዓመታት በኋላ እንደገና መታተም የጀመረው ባለፈው መስከረም ወር ነው። ታዲያ መቼ? ምንስ ተብሎ የተጻፈውን ነው "በስሕተት ላይ ስሕተት" ብሎ መተቸት የሚቻለው? በስሕተት ላይ ስሕተት የሆነውስ የጥንቱን ቤተ ጣዖት ታሪክ በቤተ እግዚአብሔር ታሪክ ላይ እንደ አሮጌ ጨርቅ ለመጣፍ ሊቁ ራሳቸው "ጋሪውን ከፊት ፈረሱን ከኋላ" አድርገው የማቅረባቸው ይዘት ነው። ይህ



www.ethiopianorthodox.org

ን ስሕተት ለማሳመን በ3ኛ መደብ ከአ ድማስ ባሻገር ተራርቆ ሳይሆን በ2ኛ መ ደብ ቃል በቃል መነጋገሩ ሳይሻል አይ ቀርምና መምህርን አንድ ቁም ነገር እ ንድናዋይዎት ይፍቀዱልን ።

ይኸውም "ተጋፊ ውሃ ሽቅብ ይፈሳ ል" ባይሉን አሁን ያሉበት የሊቃውን ት ጉባኤ ብዙ ሥራ ይጠበቅበታል ። መ ተርጐምና መታተም የሚገባቸው አያ ሌ መጻሕፍት መኖራቸውን አይርሱ ። የአንዱን ታሪክ ለሌላው በመስጠት ሐ ራምባናቆቦመርገጡንይተውትናባጠገ ብዎ ካሉት ከአንጋፋዎቹ ሊቃውንት የ ትርጉምስልትይማሩ።እንደፈሪሳዊው ካህን ራስዎትን እንደንጹሕ ሌላውን ግ ን እንደ ስሕተተኛ አድርገው በመቁጠ ር ማንጓጠጥ አይገባዎትም ። "ዘፈን የ ማያምርበት ሰው ባያለቅስ ይሻላል " እንዲሉ የጋዜጠኛነት ሙያ በተለይም የሒስ አቀራረብ ይዘት የተለየ ሙያ የሚጠይቅ ስለሆነ አንድ አዲስ ነገር

ባዩ ቁጥር ሳይመረምሩ መነሣት አያስ ፈልግዎትም ። ስለቤተ ክርስቲያናች ንም ሆነ ስለተዋሕዶ ሃይማኖታችን ደግሞ ተቆርቋሪ እኔ ብቻ ነኝ አይበሉ ።

የማንንም ስም ደግሞ በብርዕ ጫፍ መጠንቆል ይቅርብዎት ። "ረጅም ጭ ራ ከጎረቤት ያጣላ" ይባላልና ። በዕው ነት መምህርነትዎ እስኪ ይፍረድ?

እኛም ሽቅብ ቀና ብለን ይህን ሁሉ ስንመክርዎት እያዘንን ነው ። ልንተች ዎት ፈልገን የተሣን አይደለንም ። ፍሬ ነገሩ "ብነጨው ፈቱን ፥ ብደቃው ደረ ቱን" እንዲሉ ራሳችንን በራሳችን እን ደምንወቅስ ያህል ሆኖ ይሰማናል ። በ ዕርግጥ በምንሠራው ሥራ ሁሉ መቶ በ መቶ ስሕተት አይኖርም ብለን አንመካ ም ። ነገር ግን ዋናው ቁም ነገር ስልክ ደውለው እንኳ ቢነግሩን በቀላሉ ከስህ ተታችን መታረም የምንችል ስንሆን አስቀድመው ለድርጅቱ ሳያስታውቁ ያን ያህል የተምታታ ትችት ማቅረብዎ ለማነጽና ስሕተትን ለማረም መስሎ ስ ላልታየን አጸፋውን ለመስጠት ተገድ ደናል ።

# አብያተ ክርስቲያናት ድርቅን ሲቋቋሙ

*እንደ ኤ.አ. 1977 ዓ.ም በመስከረም ወር መጀመ ሪያ ላይ በኬኒያ ዋና ከተማ ናይሮቢ ውስጥ ከመቶ አገሮች የተወከሉ ብዛታቸው ወደ 500 የሚደርስ ምሁራን ፥ የተባበሩ መንግሥታት የድርቅን መስፋፋት ለመግታት በሚቻልበት ዘዴ ላይ*

እሁንም ያለፈው አለፈ ፡ እኛም በበ ኩላችን ላደረሱብን በደል ይቅርታ አድ ርገን በተለይም የሊቃውንትን ክብር ለ መጠበቅ ስንል ነው በልዝብ አጻጻፍ የ ገለጥንልዎት። ለቤተ ክርስቲያናችንና ለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታ ችን ከሆነ ግን እኛም እንደርስዎ የምን ቆረቆርላት ብቻ ሳንሆን በገቢርም ተሠ ልፈን የምንገኝ መሆናችንን እያወቁ እርስዎ ከሌላው የበለጠ እንደሚያስቡ ተሰምቶዎት "ከእናት ትሻል ሞግዚት" ለመባል ባይሞክሩ መልካም ይመስለ ናል ።

ከዚህ ጋር ዋናው የቤተ ክርስቲያናች ን ችግር በአጭር ታጥቀው ለምዕመናን ቃለ ወንጌልን የሚያበሥሩ የሊቃውን ት ቁጥር ማነስ እንጂ የተችዎች ብዛ ትማ እስካሁን ድረስ ከምልአቱ አልጎ ደለም ። ታዲያ በገዛ አረሟ እባብ ይዛ ታስፈራራ ። እንዲሉ ለምን ይሆን አን ዱ ለሌላው ጋሬጣ በመሆን ወደ ሥራ የ ተዘረጉት እጆች እንዲታጠፉ የሚያደ ርገው? "የተቀማጭ አፉ ምላጭ" ይሏ ል ይህ ነው ።

እንግዲያውስ ማዘን መቆርቆርም ብ ቻ ሳይሆን በዕውነት ለዕውነት ስለዕው ነት መሥራት ካስፈለገ የቤተ ክርስቲ ያናችንን ጐን ያደቀቀ "የሰነፍ ምላሰኛ የበሽተኛ በላተኛ" ሆኖ ከወር ወር እ ሉባልታ በማናጎድ ሀሐይ ሲሞቅ ወሬ ሲያደምቅ ቆይቶ ነፃ የወር ደመወዝ ሲ ቀበል ምንም ዓይነት የኅሊና ወቀሳ የ ማይሰማው ምድረ ዋልጌ ሲዛርፋት ገ ም ብለን መመልከቱ ነው ። ይህም ው ሎ አድሮ ሳያስፈርድብን እንደማይቀር የማያከራክር ሐቅ ስለሆነ የርስዎም የ እኛም ዘመቻ በዚህ ላይ ማተኮር የሚ ኖርበት ይመስለናል ። ተግባባን ይ ሆን?

ይነጋገርበት ዘንድ ባዘጋጀው ስብሰባ ላይ ተገኝ ተዋል ። በሰው ልጅ አለመጠንቀቅ ብቻ ሃምሣ ሺህ ስኩየር ኪሎ ሜትር የሚደርስ ለእርሻ አመቺ የሆነ መሬት በያመቱ ወደ ምድረ በዳ ነት ይለወጣል ። ዛሬ ጥረት የሚደረገው ፀም ድረ በዳነት ዳርቻ ላይ የሚገኘውን ሠላሳ ሚሊ ዮን ስኩየር ኪሎሜትር የሚደርስ መሬት ለመን ከባከብ ነው እስካለንበት መቶኛ ዓመት ፍጻሜ ድረስ ለተባለው ተግባር ወጪ ይሆናል ተብሎ የተገመተው ገንዘብ 400 ሚሊዮን የአሜሪካን ብር ማለትም የኢትዮጵያ ከ800 ሚሊዮን ብር በላይ የሚደርስ ማለት ነው ።

በዓለም አቀፍ መስክ የመጀመሪያው ደወል ያስተጋባው እ.ኤ.አ. 1973 ዓ.ም. የሳህል ድር ቅ በመላው ዓለም በተሰማ ጊዜ ነበር ። ከአም ስት ዓመት የድርቅ ሁኔታ በኋላ በተገኘው ዜና መሠረት ብዛታቸው 250.000 የሚደርሱ ሰዎ ች ሲሞቱ ፥ ወደ ሁለት ሚሊዮን የሚደርሱ ዘላ ኖች በአምሣ ፥ በዘጠናና በመቶ የሚገመቱ ከብቶቻቸውን አጥተዋል ። በሚሊዮን ሄክታር የሚገመት መሬት ወደ ምድረ በዳነት ተለው ጦአል ። ስለሆነም በሰሐራ ምድረ በዳ አካባቢ በሚኖሩ ብዛታቸው ወደ 12 ሚሊዮን በሚደ ርሱ ሰዎች ራስ ላይ የሞት ጥላ እንዳንዣበበ ይገኛል ። በናይሮቢ በተደረገው ስብሰባ ላይ የነበሩ አባላት እ.ኤ.አ. በ1973 ዓ.ም. የደረሰው አሰቃቂ ድርቅ እንደገና ይደገም ይሆናል ሲሉ አስጠንቅቀዋል ።

በስቃይ ላይ ለሚገኙት ሕዝቦች ከሚደርሰው ዓለም አቀፍ እርዳታ ሌላ ችግሩን ከሥሩ በመመ ርመር እንዴት አድርጎ ለመቋቋም ይቻላል ? የሴኔጋል ፥ የማሊ ፥ የኒጀር ፥ የላይኛው ቮልታ ፥ የማውሪታኒያና የቻድ ሕዝቦች በምን ዘዴ የሳህ ልን ምድር በተሻለ ይዞታ በተግባር ላይ ያውሉ ታል ? ስለዚህ የድርቅ መከላከል ጦርነት መነ ሻው ሊሆን የሚችለው በሳህል ቀበሌ የሚኖሩ ሰዎች እ.ኤ.አ. በ1974 ዓ.ም. ዋና ቢሮው በላይ ኛው ቮልታ የሆነ ፥ የድርቅ መከላከል ድርጅት አቋቁመዋል ። ብዙ የግል ድርጅቶችም ይህንን አቋም ረድተውታል ። ዳሩ ግን የቤተ ክርስቲ ያን ሚናስ ምን ነበር ?

እ.ኤ.አ. በ1974 ዓ.ም. በቶጎ ዋና ከተማ ሎ ሚ ላይ በዓለም አብያተ ክርስቲያናትና በመ ላው አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት በተዘጋጀው ተመሳሳይ ስብሰባ ላይ ፒዬር ከለቨር የተባለ በቮልታ የልማትና የአንድነት ድርጅት ባልደ ረባ ፥ በየስፍራው በተናጠል የሚካሄዱትን የድ ርቅ እርዳታና የልማት ሥራዎችን ሁኔታ በመ ተቸት ማስጠንቀቂያ ሰጠ እርሱ እንዳለውም የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ድርጅቶች ለሦ ስት ዓመታት እርዳታ ሲያቀርቡ ከቆዩ በኋላ ስህተታቸውን ሊያርሙ ችለዋል ።

ከዚህ በኋላ የተገኘው መመሪያ "ለ ---- ሥራ" ማለት ሳይሆን ከ --- ጋር ወይም አብረህ ጐን ለጐን ከሳህል ሕዝብ ጋር ሥራ ማለትን ሆነ የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ኮሚሲዮን ተግ ባርም ገበሬዎች ከብት አርቢዎችንና በተመ ሳሳይ ተግባር የተሠማሩትን ሰዎች ወደ መርዳቱ አተኰረ ። ይህንን ዓላማ ለማጠናከር ቀደም ሲል በየጓዱ ተቋቁሞ ከነበረው የድርቅ መከ ላከል ድርጅት ጋር የተባበረ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ድርጅት ተመሠረተ ።

ከሎሚው ጉባዔ ጀምሮ የድርጅቱ አሠራር ዓላማ በሦስት ነጥቦች ላይ ያተኰረ ሆነ ።

ሀ/ በድርቅ ቀበሌ አካባቢ የሚገኙ ሕዝቦች በቅደም ተከተል ችግራቸውን እንዲገልጹ ፥

ለ/ ከውጭ ከሚገኘው የመጀመሪያ ርዳታ በኋላ ሥራው እንደሚቀጥል ማረጋገጥ ፥

ሐ/ ጥገኝነትን የሚያስቀር የልማት ፕሮግ ራም ማካሄድ ናቸው ።

ስለተገኘው የሥራ ውጤት አሁን መናገር ጊዜው አይደለም ። ሁኖም በመካሄድ ላይ ካሉት ፕሮጀክቶች አንፃር እንደሚታየው ከሆነ ፥ ኅብ ረትና አንድነት የተቀዋሃደው አፈጻጸም ይደ ርስ የነበረውን የአየር ጠባይ ብልሹነትና ሌሎ ችንም ችግሮች ለማሸነፍ ያስችላል ። ይህም የበለጠ ፍሬ የሚሰጠው ያሉት ችግሮች በአገር ቤት ደረጃ መፍትሔ ሲያገኙ ነው ።

ለምሳሌም ያህል በላይኛው ቮልታ በአገር ቤት የሚገኙ ወጣቶች በኅብረት እርሻ ፥ የደን ልማት ፥ የግድብ ሥራና መለስተኛ የከብት ርቢ ተግባር ጀምረዋል ። ይህን ሥራቸውንም የሚ ያካሂዱት በአሮጌው ዘዴ ሳይሆን ዘመኑን በተከ ተለ አዲስ ይዞታ ነው ። ይኸው የወጣቶች ድር ጅት በቅርቡ የራሱ የሆነ የኅብረት ሥራ ለንግድ የሚውሉ የእጅ ሥራ እንዱስትሪና ፥ ዘመናዊ የከብት እርባታ ይኖራቸዋል ። ስለሆነም የያ ንጋ ሰዎች ከእንግዲህ ወዲህ ከአይቮሪ ኮስትና ከጐረቤት አገሮች ሥራ ለማግኘት ከሚጐርፉ ሰዎች ጋር አይደመርም ።

በሌላ ሥፍራ ገበሬዎች ለመቋቋም የእህል ባንክ ማዘጋጀትን በመማር ላይ ናቸው ። እነዚህ የእህል ባንኮች የሰብልን እጥረትም ለመቋቋም ይረዳሉ ። እንግዲህ ወዲህ የረሃብን ቅዠት ሊፈ ሩት አይገባም ።

ባሳህል የሚገኙ ከብቶች ብዛትና የአካባቢአ ቸው ማለትም መኖአቸውን የሚያገኙበት ሥፍ ራ ስፋት የተመጣጠነ አይደለም ። ሆኖም የከብ ቶች ይዞታው እየተሻሻለ ነው ። ገበሬዎቹ በየ ጊዜው ከብቶቻቸው ሽያጭ ገቢ ያገኙ ዘንድ በነበረው አሠራር ላይ የተመሠረተ ዘመናዊ የግ ጦሽ መሬት አያያዝ ዘዴ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል ። በዚሁ ረገድ በሰሜን ማሊ በሚገኘው በጋኦ ቀበሌ የተቋቋመው የከብት አርቢዎች የኅብረት ሥራ ማኅበር "ራስን በልማት መቻ ል" ለሚለው አሠራር መሠረቱን ጥሎአል ።

ምንም እንኳን በሳህል ላይ የደረሰውን የድ ርቅ አደጋ ፥ የዝናብ እጥረት ምክንያቱ መሆኑን በሙሉ ባይገልጥም ፥ በሳህል ላለው ሕይወት ውሃ በጣም አስፈላጊ ነገር ሆኖ ይገኛል ።

ስለሆነም ጥልቅ የሆኑ ጉድጓዶች ቆፍሮ ፥ የግድቦች ሥራና ውሃ በኩሬዎች የማጠራቀም ተግባር እየተካሄደ ነው ። ውሃ ባለበት አካባቢ ሁሉ ሠፈራ እየተስፋፋ ነው ። በሴኔጋል የሚደ ረገው የመንግሥትና የአብያተ ክርስቲያናት መደጋገፍ በሴኔጋል ላይ ለሚደርሰው ድርቅና ጊዜያዊ የውሃ ማጥለቅለ አደጋ ዋናው መፍትሔ ሁኖአል ። በአጠቃላይ የኩሬዎች ዝግጅት የው ሃ ጉድጓዶች ቁፋሮ ፥ የእርሻ ፕሮጀክቶች ዘመ ናዊ የከብት ርባታና የመሳሰሉት የልማት ሥራ ዎች ከእርሻ ተግባር ማሠልጠኛና ከጤና ጥበቃ ፕሮግራም ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ ተቋሞች ናቸው ሲል የዓለም አብያተ ክርስቲያ ናት የሚያዘጋጀው ኢ.ኤፍ.ኤር የተባለው መጽ ሔት ገለጸ ።

## ተስለህ ከማትፈጽም ባትሳል ይሻላል

ስዕለት አንድ ሰው ከሚያምንበት ነገር ጋር በሕሊናው ወይም በቃሉ የሚያደር ገው በእምነት ላይ የተመሠረተ የሕሊ ና ውል ነው ። ምናልባት አንዳንዶች ካ ለመማርናካለማወቅየተነሣለቃልቻው ለዛፉ፥ለአድባሩና፥ለአውጋሩ ፥ እየተሳ ሉ ከሰይጣን ጋር ውለታ ሲፈጽሙ ይታ ዩ ይሆናል ። እንደነዚህ ያሉት ከእምነ ት ክልል ውጭ ስለሆኑ በክርስቶስ ዘን ድ ዕድል ፈንታ የላቸውም ።

ቤተ ክርስቲያንም እንደነዚህ ያሉት ን ወደ እውነተኛው መንገድ ወደክርስ ቶስ ተመልሰው ፈጣሪያቸውን እንዲማ ጸኑ ማስተማርና መምራት አለባት ። በ እምነት ክልል ውስጥ ያሉት ክርስቲያ ኖችም ለፈጣሪያቸው ስዕለት ሲያደርጉ እናያለን ። እነዚህ ክርስቲያኖችም "በ ሚሳሉበት ጊዜ ይህንን ችግሬን ብታቃ ልልልኝ ለመታሰቢያ ይሆን ዘንድ ይህ ንን ነገር ለዚህ ቤተ ክርስቲያን እሰጣለ ሁ" ብለው ነው ከእግዚአብሔር ጋር ውለታ የሚገቡት ።

ምናልባት አንዳንዶች ያማልዱናል ብለው ተስፋ በሚያደርጓቸው ጻድቃን ና ሰማዕታት ወይም መላእክት ስም ለ ቤተ ክርስቲያን መብዓ ለመስጠት ቃ ል ገብተው ይሳላሉ ። ነገር ግን ስዕለት ና ጸሎት ተፈጻሚነት የሚኖረው እንደ ሰውየው እምነት ስለሆነ ለብዙዎች ሲ ሆንላቸው ጥቂቶች ደግሞ ልመናቸው ሳይሠምር ስዕለታቸውም ሳይፈጸም ይ ቀር ይሆናል ። እንግዲህ በእምነታቸው ጉድለት አሳባቸው ሳይሳካ በቀረ ቁጥር እግዚአብሔርን እንደማይሰማ አምላክ ወይም ሰምቶ ዝም እንደሚል እንደ አ ንድ ጨካኝ ጌታ በመቁጠር ሲያማርሩ ይታያሉ ። እንደነዚህ ያሉት ሰዎችም የራሳቸውን ስሕተት ሳይገነዘቡ በሚና ገሩት መራራ ቃል ከፈጣሪያቸው ርቀ ው በሰይጣን እንዳይፈተኑ መምከርና ማስተማር ያስፈልጋል ። "ሰውን የተሳ ደበ ኃጢአቱ ይሠረይለታል መንፈስ ቅዱስን የተሳደበ ግን ኃጢአቱ አይሠ ረይለትም" ተብሎ ተጽፏልና ። በሌላ በኩል ደግሞ ተስለው ስዕለታቸው ከተ ፈጸመላቸው በኋላ ጨርሰው የሚዘነጉ ና ነገ ዛሬ በማለትም ላለመስጠት የሚ ሞክሩ ይኖሩ ይሆናል ። እነዚህ በፈጣሪ ያቸው ላይ ያመፁ እንደ አጭበርባሪና እንደወንበዴ የሚቆጠሩ ናቸው ።

"ተስለህ የማትፈጽም ብትሆን ባት ሳል ይሻላል" ሲል ጠቢቡ ሰሎሞን የ ተናገረውም ስለዚህ ነው።(መክ.፭ ፡ ፭)

ሰዎች ስዕለት በሚሳሉበት ጊዜ የሚ ፈጽሙት ታላቅ ስሕተት አለ ። ይኸው ም ከልባቸው ጥርጣሬ የተነሣ መቼም አይሆን በማለት ሳያስቡ የማይገኘውን ነገር ሁሉ እናመጣለን ብለው መናገራ ቸው ነው ።

ለምሳሌ ይህ ነገር ከሆነልኝ የአንበሳ ደቦል ፥የነብር ግልገል መብዓ እሰጣለ ሁ ብለው የሚሳሉ እንዳሉ ይነገራል ። ይህም መቼም አይሆን የሚል ተስፋ የ መቁረጥ ሊሆን ይችላል ። ስዕለቱ በተ ፈጸመ ጊዜ ግን እነዚህን እንስሳት እን ዴት ማግኘት ይቻላል? ከአንድ ቀን በ ላይ የሆነ ጐዳና በእንብርክካችን እንመ ጣለን ብለው እየተሳሉ አንዳንዶቹ እያ ቃታቸው ሲቀሩ አብዛኞዎቹ በጉልበታ





www.ethiopianorthodox.org

ቸው ተምበርክከው የእንፉቅቅ ጉዞ ሲጓዙ የሚታዩ እንዳሉ በዓመት በዓመቱ በዚህ በታኅሣሥ ወር ወደ ቁልቢ ገብርኤል የሚሔዱ ሰዎች ይናገራሉ ። ሌላው ስሕተት ደግሞ እንደተአምር በመቁጠር አይጡን ፣ ጉርጡን ይዞ ስዕለት ነው እያሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዞ መሔድ ነው ።

እግዚአብሔር ንጹሐ ባሕርይ ጌታ ስለሆነ ለመታሰቢያ ንጹሕ ነገር እንድናቀርብለት ይፈልጋል ። በዚህ ምክንያት ነው የአቤልን መሥዋዕት ሲቀበል የቃየልን መሥዋዕት ያልተቀበለው ። ይህ ሆኖ ሳለ ለራስ ደስ የማይለውን ነገር ለእግዚአብሔር ስዕለት ነው ብሎ ማቅረብ እጅግ ሞኝነት ነው ። የአይጥ መብዓ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅሙ ምንድነው? የባሰውኑ ለአልባሳቱና ለመሳሰሉት ዕቃዎች ቀበኛ መፍጠር ስለሆነ ምዕመናን ሁሉ ሊያስቡበት የሚገባ ዋና ቁምነገር ነው ።

ወደቤተ ክርስቲያን የሚገባ መብዓ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት የሚውል ወይም ለአገልጋዮቹ ጥቅም የሚሆን መሆን እንዳለበት መገንዘብ የባለስዕለቶች ፈንታ መሆን አለበት ። ይህንንም መገንዘብ ያለባቸው ስዕለት በሚያደርጉበት ጊዜ ነው ። ያለዚያ ግን በቁልቢ ገብርኤል እንደሚታየው ድንጋይ አዛዮች አይጥና ድመት ተሸካሚዎች እየበዙ ከሔዱ የክርስትና ሕይወታችን ለአንክሮ ለተዘክሮ ብቻ ይሆንና ትርፉ ትዝብት ነው ። እንዲያውም ቅዱሱን ጌታ በማይረባ ነገር መፈተን ስለሆነ ''እህል ላበደረ አፈር ወርቅ ላበደረ ጠጠር'' እንደሚባለው እንዳይሆን ሊታሰብበት ይገባል ።

ስዕለታችን ከተፈጸመልን በኋላ የተባለውን የስዕለት መብዓ ለቤተ ክርስቲያን ለመስጠት እንዳንቸገርና ፈጣሪያችንን እንዳናስቀይም ስዕለት ከማድረጋችን በፊት ልናስታውሳቸው የሚገቡ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው ።

1 የተሳልኩትን ነገር በቅርብ ላገኘው እችላለሁ? ብሎ በቅድሚያ ማሰብ ፣

2 የተባለውን ነገር ለመክፈል የኤኮኖሚ አቅሜ ይፈቅድልኛል ወይ? ብሎ የራስን ዓቅም መገመት ፣

3 ይህ የምከፍለው ስዕለት ለቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ይጠቅማል? ብሎ ማሰብ ፣

4 ይህ የምሳለው ነገር በጥራቱ ወይም በንጽሕናው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ነወይ? ብሎ የግብር ይውጣ እንዳይሆን መጠንቀቅ ፣

5 ለእግዚአብሔር የሚሰጠው ነገር ሁሉ ያለማቅማማት በፈቃደኝነትና በቅን ልቡና መሆን እንዳለበት መገንዘብ ፣

እነዚህንም የመሳሰሉ ብዙ አስተያየቶች ሊኖሩ ይችላሉና እነዚህን ሁሉ በፊት በቅድሚያ ማሰብ ይኖርብናል ። ይህ ብቻ አይደለም የምንሰጠው ነገር (ስዕለት) ስሙ በቃላት መገለጽ ሲኖርበት እንዲሁ በደፈና እየተሳሉ ስዕለታቸው በተፈጸመላቸው ጊዜ ያልታሰበ ችግር የሚገጥማቸው ሊኖሩ ይችላሉ ።

ለምሳሌ በመጽሐፈ መሣፍንት በምዕራፍ ፲፩፡፳፱-፴ እንደምናየው በኦሪት ዘመን በእግዚአብሔር አማኝ የነበረ ዮፍታሔ የተባለ መስፍን ይህ ዓይነቱ ችግር ገጥሞት እንደነበረ ተጽፎአል ። ዮፍታሔ ወራሪ ጠላት አጋጥሞት ወደጦር ሜዳ በሚሔድበት ወቅት ''ከጠላቶቼ ከአሞን ልጆች ዘንድ በደኅና በተመለስኩ ጊዜ ሊገናኘኝ ከቤቴ ደጅ የሚመጣው ማናቸውም ለእግዚአብሔር ይሆናል ። ለሚቃጠልም መሥዋዕት አቀርበዋለሁ'' ብሎ ለእግዚአብሔር ስዕለት ተስሎ ነበር ። እግዚአብሔር ስዕለቱን ሰምቶ በጦርነቱ ሁሉ ረዳውና ድል አድርጎ ተመለሰ ። ወደቤቱም ደጃፍ በሚደርስበት ጊዜ የአባቷን በድል አድራጊነት መመለስ የሰማችው ወጣት ልጃገረድ የነበረችው ልጁ ከደስታዋ ብዛት የተነሣ ከበሮ ይዛ እየዘፈነች አባቷን ተቀበለችው ። አባቷ ዮፍታሔ ግን ድል አድርጌ በደኅና የተመለስኩ እንደሆነ በመጀመሪያ የሚገናኘኝን እሠዋለሁ ሲል ለእግዚአብሔር ቃል ገብቶ ስለነበር የሚወዳት አንዲት ልጁ በመጀመሪያ ወደሱ መምጣት ለዮፍታሔ ታላቅ ራሮት ሆነበት ። ምናልባት ዮፍታሔ ያሰበው ሰዎችን ሳይሆን እንስሳዎችን ሊሆን ይችላል ። ታዲያ ስሕተቱ ከምኑ ላይ ነበር? የቃሉ አለመወሰን ነበር ታላቅ ስሕተት ። ዮፍታሔ ''በመጀመሪያ የመጣውን ማንኛውንም'' በማለት ፈንታ በግ ፍየል ፣ ወይም ወይፈን ብሎ ገልጾት ቢሆን ይህንን ያህል ችግር ባልገጠመውም ነበር ። ይሁንና ተሳስቻለሁ ብሎ ከቃሉ ዝንፍ ሳይል የሚወዳት አንዲት ልጁን ለመሥዋዕት አቀረባት ። ይህ ዓይነቱ ስሕተትም እንዳይደረግ አስቀድሞ መጠንቀቅ ያሻል ። ከሆነ በኋላ ደግሞ እንደዮፍታሔ ቆራጥና ለፈጣሪ ታማኝ መሆን እንጂ ማቄን ጨርቄን እያሉ ምክንያት መፍጠር ተገቢ አይደለም ። ስዕለት ምን ያህል ክቡር እንደሆነ ሁላችን ልናስብበት ይገባል ።



# የመጽሐፍ ቅዱስ አምድ

## ሰላምን ትሻለህ

በዓለም ውስጥ ሕይወት ያላቸው ፍጥረታት ሁሉ ሰላምን ይወዳሉ ። ሰላምንም ለማግኘት ጥረት ያደርጋሉ ። ከሁሉም በላይ ግን የሰላምን ትርጉም በጥልቅ የሚያውቅ ፣ የሰላምን ጥቅም የሚገነዘብ የሰው ልጅ ነው ። እሱም ቢሆን ሰላም የሚገኘው በገንዘብ ብዛት ፣ በእውቀት ጥልቀት ፣ በሥልጣን ስፋትና በወገን ብዛት እየመሰለው ሲሳሳት ይታያል ። እውነተኛ ሰላም ግን የሚገኘው በእግዚአብሔር በማመንና እንደ ቃሉም በመኖር ብቻ ነው ። ይህ ሰላም ዘላቂ ነው ። አፍአዊ ብቻም ሳይሆን ውስጣዊም ነው ። ታላቁ መጽሐፍ ቅዱሳችን ስለዚሁ ርእስ ሲናገር እንዲህ ይላል ፦ ''አሁንም ከእርሱ ጋር ተስማማ ፣ ሰላምም ይኑርህ ፣ በዚያም በጎነት ታገኛለህ ። ከአፉም ሕጉን ተቀበል ፣በልብህም ቃሉን አኑር ፣ ሁሉን ወደሚችል አምላክ ብትመለስ ፣ በትዋረድም ኃጢአትንም ከድንኳንህ ብታርቅ ፣ የወርቅን ዕቃ በአፈር ውስጥ ፣ የአፈርንም ወርቅ በጅረት ድንጋይ መካከል ብትጥል ፣ ሁሉን የሚችል አምላክ ወርቅና የሚብለጨለጭ ብር ይሆንልሃል ። የዚያን ጊዜ ሁሉን በሚችል አምላክ ደስ ይልሃል ፣ ፊትህንም ወደ እግዚአብሔር ታነሣለህ ። ወደ እርሱም ትጸልያለህ ፣ እርሱም ይሰማሃል ፣ ስእለትህንም ትሰጣለህ ። ነገርንም ትመክራለህ ፣ እርሱም ይሳካልሃል ፣ ብርሃንም በመንገድህ ላይ ይበራል ። ቢያዋርዱህ አንተ ከፍ ከፍ ትላለህ ፣ ትሑቱንም ሰው ያድነዋል ። ንጹሑን ሰው ያድነዋል ፣ በእጅህም ንጽሕና ትድናለህ ።''

መጽሐፈ ኢዮብ ፳፪፡፳፩-፴

ሐዋርያው ጳውሎስም ስለ ሰላም ሲናገር እንዲህ ይላል ፦

''በቀረውስ፦ወንድሞች ሆይ ፣ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ ፣ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ ፣ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ ፣ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ ፣ ፍቅር ያለበትን ነገር ሁሉ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን እነዚህን አስቡ ፣ ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁትንም ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ ፣ የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል ።''

ፊልጵስዩስ ፬ ፣ ፱ - ፱

እንግዲህ እውነተኛ ሰላምን የሚሹ ከሆነ ዕለት ዕለት መጽሐፍ ቅዱስን ያንብቡ ። እንደቃሉም ይመላለሱ ። ያንጊዜ የእግዚአብሔር ሰላም ይበዛልዎታል በቤተሰብዎም ውስጥ ይሰፍናልና ።



ወጣቶች መጽሐፍ ቅዱስን ሲከታተሉ

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር



www.ethiopianorthodox.org

# አብያተ ክርስቲያናት በኪዩባ

የዓለም የባብቲስት ክርስቲያን አንድነት ፕሬዚዳንት ዴቪድ ወንግ ኩዩባን ከቅርብ ቀናት በፊት ጐብኝተው ነበር ። በጉብኝታቸውም ወቅት በኩዩባ ሁልጊዜ ሰኞ ሰኞ በየአብያተ ክርስቲያናቱ ከጧቱ 2፡30 ሰዓት ጀምሮ የጸሎት ፕሮግራም መኖሩን ገልጸው ፤ በተለይ የሰንበት ትምህርት ተካፋዮች ለጸሎት ከሚሰበሰቡት ምእመናን ቁጥር የበለጠ መሆኑን አስረድተዋል ። ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለግሱም ምእመናን ቁጥር ከፍተኛ ነው ሲሉ መግለጻቸውን መስከረም ወር 1970 ዓ.ም. ታትሞ የወጣው የዓለም ወንጌላውያን ኅብረት ጋዜጣ ጠቅሷል።

## በሚናፖሊስ (ሰሜን አሜሪካ) የካቶሊኮች ሰባካ ጉባዔ ስብሰባ አደረገ

ቅዱስ መጽሐፍን በሰፊው ለማስተማርና ክርስትናን ለማስፋፋት እንዲቻል የሮማ ካቶሊኮች የሰበካ ጉባዔ ከነሐሴ 20-22 ቀን 1969 ዓ.ም. ድረስ ስብሰባ አድርጐ ነበር ። ስብሰባው ያተኮረው ስለ ሥርዓተ ጥቅምት መሆኑንም በመስከረም ወር 1970 ዓ.ም. ታትሞ የወጣው የዓለም ወንጌላውያን ኅብረት ጋዜጣ ገልጿል።

ጥቅምት 10 ቀን 1970 ዓ.ም. ታትሞ በወጣው የዓለም አብያተክርስቲያናት የዜና አገልግሎት መጽሔት እንደገለጸው ዓለም አቀፍ ወሴክማ አዲስ የልማት ተራድኦ ፕሮግራም ዘርግቷል ። በዚህ ፕሮግራም መሠረት የልማት ዓላማ ከሰዎች ክብረ ሕሊና ፡ የኑሮ ሁኔታ ፡ ሰላም ፡ ፍትሕና እድገት ጋር የተዛመደ ይሆናል ። በአሠራርም የሚኖረው ተሳትፎ በየቦታው ያሉ የወሴክማ ድርጅቶችን የልማት ዕቅድ መርዳትና ማጠናከር ይሆናል ።

ይህን ለመሳሰሉ ዕቅዶችም የሚረዱ ሥዕሎችንና ጽሑፎችንም ያሰራጫል ። በዚህ ተግባር ዓለም አቀፍ ወሴክማ ብቻ ሳይሆን የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት ፡ የሳይንስና ባሕል ድርጅትም ተሳትፎ በማድረግ ላይ ነው ።

## የኡጋንዳ ቤተ ክርስቲያን መቶኛ ዓመቱን አከበረ

ከአንድ ዓመት በላይ ዝግጅት ሲደረግበት የነበረው የኡጋንዳ ቤተ ክርስቲያን መቶኛ ዓመት ክብረ በዓል የአንግሊካን ካቴድራል በሚገኝበት ናሚሬምቤ በተባለው ቦታ ተከብሯል ። ባገሪቱ ያቡብና ሰሜን ክፍለ ሀገር ያሉ ምእመናን የመጓጓዣ ዋጋና ሌላም ችግር ሳይበግራቸው ወደ ክብረ በዓሉ ቦታ በመጉረፋቸው በዓሉ እጅግ ደማቅ በሆነ ሁኔታ መፈጸሙን ነሐሴ 5 ቀን 1969 ዓ.ም. ታትሞ የወጣው የዓለም አብያተክርስቲያናት መጽሔት አብሥሯል ።



የሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የልማት ክፍል ኃላፊ ብፁዕ አቡነ ፒትሪም በአንደኑ ጉባኤ ሲካፈሉ ።

ነሐሴ 5 ቀን 1969 ዓ.ም. ታትሞ የወጣው የዓለም አብያተክርስቲያናት መጽሔት በዜና አምድ እንዳሰፈረው ከ3,000 ያላነሱ አባላት ያሉት የናዛሬን ቤተክርስቲያን በመንግሥት ታውቆ ሕጋዊ ፈቃድ አግኝቷል ። አባሎቹም እንደማንኛውም ዜጋ ሀገሪቱ የምትጠብቅባቸውን ሁሉ እንደሚፈጽሙ ታውቋል ።

## የዓለም አብያተክርስቲያናት አንድነት ሸንጐ አንድ ባንክ አቋቋመ

ይህ ባሁኑ ጊዜ 92 የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ድርጅቶች ያሉት ባንክ በ$1.103.711 መነሻ ሥራውን ሐምሌ 22 ቀን 1969 ዓ.ም ጀምሯል ። ባንኩ የሚተዳደረው በቦርድ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ዘጠኝ አባላት ያሉት ቦርድ ተቋቁሟል ። የሳሪለንካው ሚስተር አርያን ዊጀማኒ የባንኩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው ተመርጠዋል። ባንኩ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ ለሦስተኛው ዓለም አገሮች በአነስተኛ ወለድ ላንዳንድ ጠቃሚ ልማት ሥራዎች ገንዘብ ማበደር ነው ። ሐምሌ 28 ቀን 1969 ዓ.ም. ታትሞ በወጣው የዓለም አብያተክርስቲያናት የዜና አገልግሎት መጽሔት ባወጣው መሠረት የባንኩ ዋና ሥራ አስኪያጅ እስከ አሁን ከአፍሪቃ 13 ከእስያ 10 ከላቲን አሜሪካ የብድር ጥያቄ የቀረቡ መሆናቸውን ገልጸዋል ።

## ፓትርያርክ ፒሜን ቁስጥንጥንያን ጐበኙ

በኢኩሜኒካል ፓትሪያርክ በአቡነ ዲሚትሮስ ጋባዥነት የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ፒሜን ቁስጥንጥያን ለ9 ቀናት ጐብኝተዋል ። ጥቅምት 9 ቀን 1970 ዓ.ም. በወጡት የጋራ መግለጫ ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ያላቸውን ግንኙነት ይበልጥ ለማሻሻል ማቀዳቸውንና በዓለም አብያተ ክርስቲያናት አንድነት ሸንጐም ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ እንደሚያጠናክሩ ገልጸዋል ። የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የአንድነት ሸንጐ መፈጠርና ከሌሎች ክርስቲያኖችም በውይይት መቀራረብ አስፈላጊ ስለመሆኑ ሁለቱም ፓትርያርኮች አምነውበታል ። ከሌላ ሃይማኖት ተከታዮችም ጋምር መልካም ግንኙነት መፍጠር ተገቢ ስለመሆኑም ተነጋግረዋል ሲል ጥቅምት 17 ቀን 1970 ዓ.ም. የወጣው የዓለም አብያተክርስቲያናት የዜና አገላግሎት መጽሔት አብሪርቷል ።

## ለአታሚዎች ሴሚናር ተሰጠ

ከልዩ ልዩ አገሮች ለተውጣጡና ከአብያተ ክርስቲያናት ጋር ግንኙነት ላለቸው የሕትመት ሥራ ኃላፊዎች ለንደን ከተማ አጠገብ በሚገኘው በሮያስ ሆልወይ ኮሌጅ ሴሚናር ያካሄደው ዓለም አቀፍ የክርስቲያን ግንኙነት ማኅበርና አንድ በእንግሊዝ አገር የሚገኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሥነጽሑፍ ማደራጃ ጽ ቤት ናቸው ። በሴሚናሩ የተነሱት ዋና ዋና ሃሳቦች የመጻሕፍት ዝግጅት ፣ ሕትመት ፣ ማከፋፈልና አያያዝ ነበር ። በነዚህም ላይ ብዙ አዳዲስ አሳቦች ቀርበው ውይይት ተደርጐባቸዋል ፡ ምንም እንኳ ሴሚናሩ ገና ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገ ቢሆንም ብዙ መቀራረብን እንደሚፈጥር ታምኖበታል ። ለዚህ ሴሚናር ከአፍሪቃ 9 ከእስያ 6 ከላቲን አሜሪካ 2 ከመካከለኛው ምሥራቅ 1 ከምሥራቅ አውሮጳ 5 በጠቅላላው 23 ተወካዮች የተገኙ መሆኑን በመስከረም ወር 1970 ዓ.ም. ታትሞ የወጣው የዓለም አቀፍ ክርስቲያን ግንኙነት ማኅበር ጋዜጣ ገልጿል

## ተዘግቶ የኖረው የሉተራውያን ቤተ ክርስቲያን እንደገና ተከፈተ

ፍራንክፈርት ከተማ ከሚታተም ከአንድ መጽሔት የተገኘ ተብሎ መስከረም 27 ቀን 1970 ዓ.ም. ታትሞ በወጣው የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን ጋዜጣ እንደተጠቀሰው አንድ ከሌንግራድ ከተማ (ሩሲያ) 20 ኪሎሜትር ርቆ የሚገኝ የሉተራውያን ቤተ ክርስቲያን እንደገና ተከፍቷል ። ከ1926 ዓ.ም. ጀምሮ ተዘግቶ የነበረው ቤተ ክርስቲያን ባለፈው ዓመት በሶቭየት ኅብረት የመንግሥት ባለሥልጣኖች ተመዝግቦ ሥራውን ጀምሯል ።

## ዓለም አቀፍ ወሴክማ በልማት መስክ

# የጅማ ጉብኝት

በጅማ ከተማ ሰባቱን አብያተ ክርስቲያናት የሚወክል አንድ ንዑስ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ኮሚቴ በቅርቡ ተቋቁሞ ሥራውን በመጀመር የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርን ዓላማና የኮሚቴውን አቋም ለምእመናን እንዲገልጹልን ብለው የማኅበሩን ዋና ጸሐፊ ስለጋበዙ ጥቅምት 13 ቀን 1970 ዓ.ም. በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌል በተደረገው ታላቅ ስብሰባ ላይ ተገኝተው አቶ ኃይሉ ወልደ ሰማያት ፡ የማኅበሩ ዋና ጸሐፊ ፣ ስለማኅበሩ ሥራ ሰፊ ገለጣ አድርገዋል ። የተቋቋመውን ኮሚቴም ለሕዝቡ አስተዋውቀው በተመደቡበት ኃላፊነትም እንዲተባበሩአቸው አደራ ብለዋል ። በዓሉን ምክንያት በማድረግ በዚህ ቀን ለተሰበሰበው ሕዝብ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ታላቅ ቅናሽ በማድረግ እንዲገዙ አድርገዋል ። ብዙዎችም የማኅበሩ አባል ሆነው ተመዝግበዋል ፡ አባል የነበሩትም የ1970 ዓ.ም. አባልነታቸውን አድሰዋል ።

ጥቅምት 12 ቀን 1970 ዓ.ም. የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናትን ድርጅቶችና ሥራ በመጐብኘት ዋና ጸሐፊው ከአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጋር ተነጋግረዋል ።

በሌሎችም ክፍላተ ሀገር እንዲህ ያለው መተባበር እንዲደራጅም ምእመናን እያበረታታን ተደርጐም ለማየት በጉጉት እንጠባበቃለን ።

በጅማ የተቋቋመውን አዲሱን ንዑስ ኮሚቴ እግዚአብሔር እንዲጠቀምበትና ጥበቡንም እንዲያጐናጽፈው በጸሎታችሁ እንድታስቡት አደራችን የጠበቀ ነው ።


የንዑስ ኮሚቴው አባሎች ስም ዝርዝር

1. አቶ ገርማ ጽጌ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
2. አቶ ጌታሁን ፀጋዬ ከመካነ ኢየሱስ
3. አቶ ተክሌ ፍስሐ ጽዮን ከቃለ ሕይወት
4. አቶ መቻል ባልቻ ከሙሉ ወንጌል
5. አቶ ባርናባስ ገ ማርያም ከካቶሊክ
6. አቶ አሸናፊ ኢሳይያስ ከሕይወት ብርሃን
7. አቶ ሰሎሞን ገነቱ ከአድቬንቲስት ናቸው

## አብያተ ክርስቲያናት .......

## በአውስትራሊያ የሉተራውያንና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ውይይት ውጤት አስገኘ

በአውስትራሊያ የሚገኘው የሉተራውያን አጠቃላይ ጉባኤና የኤፒስ ኮፖል የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሥርዓተ ጥምቀት አፈጻጸም በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተ መሆኑን ሁለቱም አብያተ ክርስቲያናት ተቀብለው በሥርዓተ ጥምቀት አፈጻጸም በመካከላቸው የነበረውን ልዩነት አስወግደዋል ሲል የዓለም ሉተራውያን ፌዴሬሽን ጥቅምት 10 70 ያሳተመው ጋዜጣ ገለጸ ።



ከስብሰባው ወጥተው መጻሕፍትን ሲገዙ





www.ethiopianorthodox.org

ሰልደት በዓል
ታሳቅ ቅናሽ



# በአካለ ስንኩላን
# የተሠሩ ውብ
# የስጦታ ዕቃዎች

አካለ ስንኩላን ምን ያህል ራሳቸውን ለመርዳት እንደሚሞክሩ ተመልክተዋል ?

የሀገር ጥበብ መደብር ውስጥ ብሔራዊ ቲአትር ፊት ለፊት በሚገኘው ሱቃችን ለልደት በዓል ሽያጭ ያቀረብናቸው ዕጹብ ድንቅ ዕቃዎች የአካለ ስንኩላን የረቀቀ የሥራ ውጤት ናቸው ።

ይጐብኙን ! በሚመለከቱት ሁሉ እንደሚደሰቱ እናረጋግጥልዎታለን !

★ ከንጹህ ሱፍ የተሠሩ ሥጋጃዎች
★ የሙሽራ ልብስ
★ የወንድና የሴት ልብስ
★ የሕፃናት ልብስ
★ የጠረጴዛ ልብስና ለመጋረጃ የሚሆኑ ጨርቃጨርቆች በየዓይነቱ ይገኛል ።



ያስታውሱ

ከመደብራችን የሚገዙት ዕቃ ሁሉ ለአካለ ስንኩላን አለኝታ ነው




ተጨማሪ የሺያጭ ቦታዎች

- ላም በረት በሚገኘው ዋና ፋብሪካ
- አፍሪካ አዳራሽ መደብር ናቸው

የሀገር ጥበብ መደብር የቀድሞ ተክሉ ደስታ ሕንፃ
የመ. ሣ. ቁ. 30722 ስልክ ቁ. 152464


www.ethiopianorthodox.org



# የምእመናን ድምጽ

ቤተ ክርስቲያን አንዲት ስትሆን የአስተዳደሩ መዛባት እንደ ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ያላት ሌላዋ ምንም የሌላት በመሆኗ የሚተያስባት ጧፍ ሻማ እንኳን ከአላቸው አብያተ ክርስቲያናትና ምዕመናን በአስተዋጽኦ ነው ። አቶ ለገሠ ወልድ የዛሬዪቱን ቤተ ክርስቲያን ለማሻሻል ምን ዓይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል ይላሉ?

—በክርስቶስ የተመሠረችው ቤተ ክርስቲያን አንዲት መሆኗን ገልጸውታል ። ገንዘቧም ሀብቷም ምእመናን እንደነበሩ በሐዋርያት ዘመን የነበረው የእምነት ተግባር እንደሚያስረዳው ሁሉም ክርስቲያኖች ሠርተው የሚያገኙትን በሐዋርያት እግር አጠገብ አስቀምጠው ለአስፈላጊው ቦታ እንደሚያውሉት ግልጽ ነው ።

እንደ ቤተ ክርስቲያን ሀብት ሲኖራት ሌላዋ የላትም ለተባለው እንዲያውም ሀብት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ራሳቸውን ችለው ለሌላው መርዳታቸው ያስመሰግናቸዋል ይመስለኛል ። ለዛሬዪቱ ቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት ሰበካ ጉባኤ በማቋቋም ምእመናንና ቤተ ክርስቲያንን እንደድልድይ ሆነው የሚያገናኙ የሰለጠኑ ሰባክያን ያስፈልጓታል ። ይህ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ራሷን ለማስቻል ጊዜ አይወስድም እላለሁ ። • • • •

አቶ ዮሐንስ መብራቱ ብዙ ጊዜ የውጭዎቹን አብያተ ክርስቲያናት አስተዳደር ተመልክተዋል ። ምናልባት ለእኛም ለዛሬዪቱ ቤተ ክርስቲያን እንዲረዳት አንዳንድ ጥቆማ ቢያደርጉልን?

— አብያተ ክርስቲያናት የሚተዳደሩት በምእመናን ነው ። መቼም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ጽሑፍና የቅርሳቅርስ ባለቤት ስለሆነች ውለታዋ የሚዘነጋ አይደለም ። እኔ እንደሚመስለኝ በአስቸኳይ ራሷን ማስቻል መልካም ነው ።

የውጭዎቹ ምእመናን ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቷት እንደ ቤተ ሰቦቻቸው ነው ። ለምሳሌ ሁለት ቤተ ሰቦች ያሉት ሦስተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ናት በዚሁ ዓይነት እየሠሩ ነው ለሌሎች ርዳታ ለመለገሥ የሚበቁት በመሠረቱ እኔ እንዳየሁት ለሃይማኖት ተናተኛ እንደኢትዮጵያ ምእመን ያለ ሕዝብ አይገኝም ። ችግሩ አስተናባሪ የሌለው በመሆኑ ለቤተ ክርስቲያን የሚፈለገውን ያህል ርዳታ ሲሰጥ አይታይም

እንጂ ወደጸሎት ቤት በሄደ ቁጥር እጁ ምጽዋት ከመስጠት መች ይቆጠባል ።

በመጨረሻ ላስታውሳችሁ የምፈልገው ይህ ድርጅት ርምጃውን ወደኋላ ሳይል የምእመናን ድምጽ ያስተጋባ ራስን መቻል የሚመጣው ከሥራ ፍሬ ነውና ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org